# ልጆችን

# ወደ እውነት መምራት

በዓለማየሁ ማሞ

ለጥያቄ ወይም አስተያየት

የጸሐፊው አድራሻ፣

ዓለማየሁ ማሞ

1123 Nicholas Drive

Wheaton, MD, 20902 USA

ስልክ:- 240 - 355-9591

ኢ-ሜይል:- a_mamo@hotmail.com

የመጀመሪያ እትም 1993 ዓ.ም (2000)

2ኛ እትም 1998 ዓ.ም (2005)

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሽፋን ዝግጅት:-

ብዙአየሁ አበበ

እርማት:-

ሩት መኮንን

ገዛኸኝ አንበሉ

ዘነበ ገብረሐና

የኮምፒውተር ሰቀማ:-

መሠረት አበበ

ዓለምፀሐይ እውነቱ

የኅትመት ዝግጅት:-

ፕሮፌክሽን ቢዝነስ ሴንተር እና

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

የ2ኛው እትም አሳታሚ፣

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

# ማውጫ

ገጽ

1. የቀዳሚ አንባቢያን አስተያየት ........ 4

2. መንደርደሪያ ........ 9

3. ጥቂት ስለ ልጆች ........ 19

4. መጪው ትውልድ ........ 29

5. ስለ እነርሱ መጸለይ ........ 35

6. ልጆችን ወደ እውነት መምራት ........ 47

7. ማስተማርና ማሠልጠን ........ 56

# 1

## የቀዳሚ አንባቢያን አስተያየት

እግዚአብሔር አብርሃምን ለምን ባርኮ የበረከት ምክንያት እንዳደረገው ሲመሰክርለት፣ «ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና» (ዘፍጥ. 18:19) ነበር ያለው:: ዛሬም ልጆቻቸው ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ እንዲያድጉላቸው ለሚሹ ወላጆች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የሰንበት ት/ቤት አስተማሪዎች እንዲሁም ለምእመናን ሁሉ ይህ መጽሐፍ ተግባራዊ መመሪያን የሚሰጥ እጅግ ጠቃሚ መሣሪያ እንደሚሆን ትልቅ እምነት አለኝ::

ገዛኸኝ ሙሴ

(ከወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ)

መጽሐፉ ከችግሩ ተነሥቶ ወደ መፍትሔው ያመራል፤ ለልጆች የምናስተምረው ብቻ ሳይሆን ከእነርሱም የምንማረው እንዳለ በበቂ ይገልጻል:: አገርን ተረካቢ መጪው ትውልድ ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለምድራችን እነርሱን እንዴት መቅረጽ እንዳለብን ስለሚያሳይ ሁሉ ሰው አንብቦ ቢጠቀምበት እላለሁ::

ወንጌላዊ መድኅን ገ/ሥላሴ

(በኢ.አ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ)

ይህች መጽሐፍ ጥሩ ይዘት አላት፤ ለወላጆችና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ሕፃናት ያላቸውን የአመለካከት አድማስ የምታሰፋና ስለ ነገ እንዲጨነቁና እንዲያስቡ የምታደርግ ሆና አግኝቻታለሁ:: በዚህም ረክቻለሁ:: ለሕፃናት አስተማሪዎችም ሥልጠና መርጃነት ታገለግላለች ብዬ አስባለሁ::



ይልቁንም ለብዙው ሰው ግምት ሩቅ ቢመስልም፣ ነገን በዛሬው ዕይታ በማማተር ልጆቻችን ምን ሊመስሉ እንደሚገባቸው የምታሳይ በመሆኗ ሊበረታታ የሚገባው ነው::

ገነት ጫኔ

(ከኅብረት ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን)

የልጅ ነገር ሆድ ይቆርጣል፤ ባወጣ ያውጣው የምንተዋቸው ፍጡራን አይደሉምና:: ቅዱሳን መላእክት ይከበቧቸው፣ ርኩሳን አጋንንት የሚወስነው በከፊል በሚያሳድጋቸው ቤተሰብ፣ ቤተ ትምህርት፣ ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ዙሪያ ገባው ሁሉ ነው:: ይህች መጽሐፍ ሁላችንም ያለብንን ኃላፊነት እያሳሰበች መንገዱንም እየጠቆመች የማያልቀውን የመለኮት ተስፋ ትፈነጥቃለች:: መነበቧ ልባም ያደርጋል::

ንጉሤ ቡልቻ

ከቃለ እግዚአብሔር አንባቢዎች ማኅበር

*ልጆችን ወደ እውነት መምራት* በሚል ርእስ የቀረበው ይህ መጽሐፍ በአገራችን አብያተ ክርስቲያናት አስፈላጊ ትኩረት ያላገኘውን የልጆችን አገልግሎት ጠበቅ እንድናደርግ የሚያነቃቃ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሳይንሳዊ (ተፈጥሮአዊ) የሆኑ እውነታዎችን አጣጥሞና አጫጭር ገጠመኞችን አካትቶ የቀረበው ይህ አነስተኛ መጽሐፍ መሠረታዊ እውነቶችን መጽፉፍ መሠረታዊ እውነቶችን አልፎ በመስኩ ሰፊና ጠለቅ ያለ ሥራ እንዲሠራም ፈር ይቀዳል::

ናሁሠናይ አፈወርቅ

የሥነ ጽሑፍ ባለሙያ

(ከመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን)

ከምንም በላይ ስለዚህ ጽሑፍ እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግናለሁ:: በማስከተልም ይህንን ጽሑፍ ሳነብ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ተግባራዊ የምናደርጋቸውን ትውልዳችንን የሚታደጉ አሳቦችን አሳይቶኛል:: ይኸውም የመጀመሪያው ነገር እኛ ከወላጆቻችን ልናገኝ የሚገባንን በማጣታችን ትውልዱ እስኪጠፋ ድረስ የተጎዳንበትን ነገር በምንወልዳቸውና በተወለዱት ልጆች እንድንክስ ነው:: ይህም ማለት እኛ ቤተሰብን የምንመሠርተው ልጆችን በሥጋ ለመውለድ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመንፈስም፣ በአመለካከትም ሁሉ ወልደናቸው ወደ ክርስቶስ ቤተሰብ እንድንቀላቅላቸው፣ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚመስል ትውልድን እንድናተርፍ ነው::

ሁለተኛው ደግሞ በጣም አስረግጬ ማሳሰብ የምፈልገው ነገር በዚህ ወቅት በጽሑፉ ላይ እንደተገለጠው በአገራችን ቢሆን በዓለማችን በጣም ብዙ ሕፃናት በየመንገዱ ወድቀው በማይገባቸው (በሚዘገንን) ሁኔታ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ:: ዛሬ ነፍሳቸውን የሚታደጋት ጠፍቶ ታጣጥራለች፤ ስለዚህ ለእነዚህ ልጆች መድረስ የሚገባን እኛ መሆናችንን አውቀንና ተረድተን ፈጣን እርምጃ እንድንወስድ እግዚአብሔር በዚህ ጽሑፍ የጊዜውን መልእክቱን ይነግረናል:: ይህ ደግሞ ነውር የሌለበት በእግዚአብሔር ፊት ቀጥ ብሎ የሚወጣ ትክክለኛ መሥዋዕትና አምልኮ ነው (ያዕ. 1:27)::

ስለዚህ ይህንን ጽሑፍ አንብበን ተግባራዊ ብናደርገው የአንድ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን የምድራችን ታሪክ እንደሚለወጥ አልጠራጠርም::

ዘማሪ ሩት መኮንን

(አ/አ መካነ ኢየሱስ)



ዛሬም እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነው የእግዚአብሔር ዕቅድ በታላላቆች ብቻ ሳይሆን በብላቴኖችም ላይ ነው:: ታዲያ ይህን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተረድተን ልጆቻችንን በቃሉና በጸሎት ከብበን በዙሪያቸው ሰይጣን ካስቀመጠው ወጥመድ አምልጠው ለነገ ይበቁ ዘንድ የሚረዳ፤ ክርስቲያን ወላጆችንም ልክ እንደ እነርሱ ልጆቻቸው ጌታን እንዴት መከተል እንደሚችሉ በተጨባጭ ምሳሌዎች የሚያስተምር መጽሐፍ ነው::

በአገራችን በቂ የሆነ ትኩረት ባልተሰጠው ልጆችን ወደ እግዚአብሔር እውነት በመምራት በዚህም እውነት ጸንተው እንዲኖሩ በማድረግ አገልግሎት ላይ ያሉትን ሁሉ የሚጠቅምና የሚያስተምር ለበለጠም አገልግሎት የሚያነሣሣ መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ::

ወንደም ገዛኸኝ አንበሉ

ከአ/አ/ዩ የእንግሊዘኛ ዲፓርትመንት

ከወንድም ዓለማየሁ ማሞ ጋር ከተዋወቅን በጣም አጭር ጊዜአችን ነው:: ይሁን እንጂ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ በርካታ ሥራዎችን አብረን ሠርተናል:: በዚህ ወቅት ዓለማየሁ በዓለም የነበረውንና ሊያገኝም ይችል የነበረውን ክብር እና ጥቅም በእምነት መተዉን ተረድቻለሁ:: ወንድማችን የእምነትና የጸሎት ሰው ሲሆን፣ ለክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ዕድገት ባለው ቅንዓት በአርታዒነትና በተርጓሚነት ሥራ ተሰማርቶ ይገኛል::

እነሆ፣ *በየብርታቱ ምሥጢር* አህዱ ብሎ፣ *ጸሎት ሲተነተንን* ከደገመ በኋላ፣ አሁን ደግሞ የሦስተኛ ሥራውን ትኩረት በልጆች ሕይወት ላይ በማድረግ አዘጋጅቶልናል:: ይህ የልጆች ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ቢሆንም፣ ብዙም ያልተዳሰሰ ነው:: በጊዜው ነቅተን ማድረግ ያለብንን ካላደረግን ደግሞ የከፋና የባሰ ጥፋት ከፊታችን ተደቅኖ ይጠብቀናል:: ስለዚህ ዘመኑን ለመዋጀትና ልጆችንም ለመቤዠት

የሚያስቡና የሚያልሙ ወላጆች፣ የሰንበት ት/ቤት መምህራን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች፣ በልጆች አገልግሎት የተሰማሩና ሌሎችም ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ አካላት በሙሉ ይህንን የኅትመት ሥራ ውጤት በጥንቃቄና በማስተዋል እንዲጠቀሙበት እመክራለሁ::

ዘነበ ገብረሐና

የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ኃላፊ



# 2

# መንደርደሪያ

- በዛሬዋ ቀን ከ35,000 የሚበልጡ ሕፃናት በምግብ እጦት ይሞታሉ::
- በዓለማችን ዙሪያ 100 ሚሊዮን የሚሆኑ ልጆች በሕገወጥ መንገድ ተቀጥረው በከባድ ሥራ ጉልበታቸውን እየተበዘበዙ ነው::
- በየዓመቱ 4 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናት ወደ ዝሙት አዳሪነት ሲሰማሩ፣ በዚህ ወቅት 100 ሚሊዮን ሕፃናት አሳዳጊና መጠለያ አልባ ወይም በዘመኑ ቋንቋ «የጎዳና ተዳዳሪ» ናቸው::
- በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት የትምህርት ዕድል አላገኙም፤ ከእነዚህ ውስጥ 2/3ኛ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው::

* * *

«በመንገድ ተራብኩ፤ ተጠማሁ፤ ግን መፍትሔ አልነበረም:: የጥይት ሙዚቃ ሰልችቶኛል:: ቤቴንም እናፍቃለሁ:: ይህ መከራ በእኔና በቤተሰቤ ላይ ለምን እንደ መጣ አላውቅም::» ይህን የተናገረው በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ የጦርነት ሰለባ ከሆኑት ሕፃናት አንዱ የሆነው የ10 ዓመት ሕፃን የቦስኒያ ፔትሮቫክ ነዋሪ ዓሊ ነው::

ለእንግሊዝ ቀይ መስቀል በሰጠውና ድርጅቱም አባዝቶ በበተነው የእጃችሁን ዘርጉ ካሴት ላይ ዓሊ መራራ ትዝታውን እንዲህ ይናገራል::

«ሁሉም ነገር ጥሩ ነበር:: በዕለተ ዓርብ ከወንድሜና እኅቴ ጋር ከትምህርት ቤት ተመለስን:: ቀጥሎም ከጎረቤት ጓደኛዬ

ጋር ኳስ ስንጫወት ቆየን:: ቤት ስንገባ እማማ የተፈጨ ሥጋና ድንች አቀረበችልን:: እንደገናም ባቅላባ ጨመረችልን:: ግሩም ምግብ ነበር:: ደስታችን ግን እስከሚቀጥለው ቀን አልቆየም:: በእንቅልፍ ላይ እያለን አገር ተደበላለቀ:: በዚህም መሐል በራችን ተንኳኳ፤ የማላውቃቸው ሰዎች አባቴን እያዳፉ ወሰዱት:: ከዚያ ወዲህ አላየሁትም:: ይሙት ይኑር አላውቅም:: በመቀጠልም ሠፈሩን መልቀቅ የግድ ሆነ:: ከየቤቱ የሚወጣው የሰው ጠብታ ተጠራቅሞ ወደ ስደተኞች ወንዝ ተቀየረ:: ለ24 ቀናት በእግር መጓዝ ነበረብን:: አሁን በመጠለያ ታጉረናል:: መጨረሻችን ምን ይሆን?» ይላል::

ሕፃኑ ዓሊ ጦርነት ለምን እንዳስፈለገ አይገባውም:: ግን አንድ ነገር ያውቃል:: ትናንት ወዳጆች የነበሩ ዛሬ ደመኛ ናቸው:: ቤተሰቦች ተለያይተዋል:: ብዙ ሺህ ሰዎችም ሞተዋል::

በፖፑስ መጽሔት የጥቅምት 1989 (እ.ኤ.አ) እትም ላይ አሳዛኝ ታሪኩ የተገለጸው ዳንሰን ኪሊማ ደግሞ 13 ዓመቱ ነው:: ወላጆቹ በኤድስ ከሞቱ በኋላ ከእርሱ በዕድሜ የሚያንሱ ስምንት እኅቶቹና ወንድሞቹ ያለአሳዳጊ ቀርተዋል:: እናም ባከባ በምትባለው የታንዛኒያ የገጠር ቀበሌ የካሽኔ መንደር ኗሪ የሆነው አያታቸው ያስጠልላቸው ዘንድ ግድ ሆነ::

«ሕፃናቱ ደልቷቸው አይኖሩም፤ ምክንያቱም እኔ ያረጀሁ ስለሆንኩ ገቢዬ አያስመካም» የሚለው የ68 ዓመቱ አያት፣ ከእነዚህ ሌላ በወንድ ልጁ ሞት ሳቢያ ተጨማሪ አምስት ሕፃናትን እያሳደገ ነው::

ኢማኑኤል ኪሊማ (አያት) ከቡና ሽያጭ በዓመት 100, 000 የታንዛኒያ ሽልንግ ያገኝ ነበር:: አሁን የሚያገኘው ግን 15,000 እንኳን አይሆንም:: (ይህ ወደ አሜሪካ ዶላር ሲመነዘር 100 ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ብር ደግሞ 850 ብቻ ይሆናል::)



ዳንሰን ከሕፃናቱ ውስጥ ትልቁ እንደ መሆኑ የመማሩን ጉዳይ እርግፍ አድርጎ ትቶ ሥራ ለማግኘት እየሞከረ ነው፤ ግን አልተሳካለትም:: ለምን ቢሉ ወላጆቹን የገደለ በሽታ በቀጣሪዎቹ አእምሮ ተቀርጾ አላስፈላጊ የሆነ ፍራቻ አሳድሯል::

«ባለፉት ሦስት ዓመታት ብዙ ተምሬአለሁ:: ኤድስ አሳፋሪ ነገር ነው:: እኔንም ሌሎች የሚያዩኝ በዚሁ መነፅር ነው፤ በወላጆቻችን ሞት የእኛ እጅ ነበረበት እንዴ?» ይላል ዳንሰን በአሳዛኝ ድምፅ::

ግን አሥራ አራቱም ልጆች በአንድ ነገር ይጽናናሉ:: ይኸው መገለላቸው ይበልጥ አፋቅሯቸዋል:: «በጣም እንዋደዳለን:: ምናልባትም ተመሳሳይ ችግር ስላለብን ይሆናል» ብሏል ዳንሰን ኪሊማ::

ወደ ዩክሬይን ስንሻገር የሕፃናት የነርቭ ሐኪም (ኒውሮሎጂስት) የሆነችው ዶክተር ኤሊና ጋሊና በአዴሳ በ1986 (እ.ኤ.አ) በደረሰው የቸርኖቢል የኃይል ማመንጫ ፍንዳታ ሳቢያ የጤና መታወክ የደረሰባቸውን የዛሬ አበባዎች ለመርዳት ስትሠራ ቆይታለች::

ጥሪ ለሕፃናት የተሰኘው መጽሔት በነሐሴና መስከረም 1993 (እ.ኤ.አ) እትሙ ስለተረሱት የቸርኖቢል ሕፃናት ባሰፈረው ጽሑፍ ሐኪሟ አሁን አሁን ፍንዳታውን የሩቅ ትዝታ አድርጎ ለማየት ከሚቻልበት ወቅት ላይ ተደርሷል ለማለት እንደሚቻል ተናግራለች:: ይህን ከማለቷ በፊት ግን ቢያንስ 2000 ሕፃናትን አክማለች:: አሁንም ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት ረዥም ጊዜ እንደሚፈጅ ትገልጻለች::

«ሕፃናቱ ወደ እኛ ኢንስቲትዩት ይመጡና ሻል ሲላቸው ወደ ቤታቸው እንልካቸዋለን:: ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን? ከቤተሰብ ለይተን ደህና ቦታ እናኑራቸው? ሕዝቡን በሙሉ ወደ ሌላ እናጓጉዝ ወይስ አካባቢውን ለማደስ ሌላ ዘዴ እንፍጠር?» የዶክተሯ መደምደሚያ::

የ13 ዓመቱ ኢማኑኤል አንቶኒዮ አልቤርቶ ደግሞ አባቱ በልጅነቱ የሞተበት ሕፃን ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት እናቱ የአንጎላ መንግሥት ጦርና ተቀናቀኝ ዩኒታ ክፉኛ በሚዋጉበት ጊዜ ከሁዋምቦ ወደ ሉዋንዳ ሸሸች። እዚያም የአእምሮ ሕመምተኛ ሆነች። ኢማኑኤል ያን ጊዜ የነበረው ዕድል ቀን በጎዳና እየዋለ ማታ ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ማደር ነበር።

- *ይህ በአንድ ወቅት በሕፃናት ሕይወት ላይ ለሚያተኩር መጽሔት አቅርቤው ከነበረ ጽሑፍ የተቀነጨበ ነው። ሰቆቃው በዚህ አያበቃም፤ ይቀጥላል።*

በደቡብ አሜሪካ ብራዚል ብዙ ልጆች ትምህርት ቤት በሚጀምሩበትና በመጫወቻ ጊዜአቸው ቀኑን ሙሉ ወደ 12 ሰዓት የሚደርስ ሥራ በመሥራት ያሳልፋሉ። ሠርተውም የሚያገኙትን ገቢ ለቤተሰቦቻቸው መስጠት አለባቸው።

በጣም የሚያሳዝኑት በደቡብ ብራዚል የማዕድን ማውጫ፣ በብርቱካን እና በቡና ለቀማ ሥራ የሚሰማሩት ሕፃናት ናቸው። መንግሥታዊ ከሆነ ምንጭ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በዚህች አገር 7 ሚሊዮን የሚሆኑ ዕድሜያቸው ከ5-17 ዓመት የሚሆኑ ሕፃናት እና ወጣቶች ከዕድሜአቸው በላይ ከባድ በሆነ ሥራ ተጠምደው ይገኛሉ።

ሪይና የ15 ዓመት ልጅ ናት። የዕድሜዋን ግማሽ ያሳለፈችው በዝሙት አዳሪነት ነው። እንደ እርሷ ያሉ ሕፃናት ለኤች አይ ቪ ቫይረስ የተጋለጡ ናቸው። ስለዚህ ጉዳይ ያላትን አመለካከት ሪይና ስትናገር፣ «እኔ ዛሬ ማታ ልሞት እችላለሁ፤ ታዲያ ገና ለገና የዛሬ ዓመት እሞታለሁ ብዬ ምን አስጨነቀኝ?» ብላለች።

በጓቲማላ የፍራንሲስኮ አባት፣ «የሚያስፈልገንን ነገር ገዛዝቼ ልምጣ፤ አንተ እዚህ ጠብቀኝ» ብሎት ወደ ሱፐር ማርኬት ገባ። ፍራንሲስኮ ሳምንቱን ሙሉ በር ላይ ሆኖ



በሰቀቀንና በጭንቀት ጠበቀ። ከአንድ ሳምንት በኋላ አባቱ ጥሎት መጥፋቱን ተረዳ።

አንድ ቀን አንድ ትንሽ የጎዳና ተዳዳሪ ልጅ ወስዶ ከጓደኞቹ ጋር አስተዋወቀው። እነዚህም ልጆች ፍራንሲስኮን እንዴት መስረቅ፣ መለመን፣ መኪና ማጠብና መጠበቅ እንደሚቻል አስተማሩት። ከእነዚህም ነገሮች ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ከቡድኑ ጋር መካፈል የቡድኑ ሕግ ነው።

«ለረዥም ጊዜ ኑሮዬ ግቡን ያልመታ ሩጫ ነበር፤ የተለያዩ ዓይነት ደንበኞች ነበሩኝ። ራሴን ለመግደል ሞከርኩ፤ ግን አልተሳካልኝም። ደስተኛ ስላልነበርኩ በአደገኛ ዕፆች ራሴን አሰመጥኩ፤ ስለ ነገ አላውቅም፤ ከሚቀጥለው ልደቴ በፊት ግን መሞት እፈልጋለሁ» ሲል አንድ የፊሊፒንስ ልጅ ተናግሯል።

በእንግሊዝ አገር ውስጥ ካሉት 3.5 ሚሊዮን ልጆች 1000 የሚሆኑትና ከ16 ዓመት በታች ያሉት የ16 ዓመት ልደት በዓላቸውን ከማክበራቸው በፊት አሥር ጊዜ ከቤታቸው እየጠፉ ይወጣሉ።

በኢጣሊያ ሲሲሊ ከተማ ውስጥ ከ5-14 ዓመት የሚሆናቸው ሕፃናት ሴቶች ልጆች በዝሙት አዳሪነት ሥራ ተሰማርተው ይገኛሉ።

እነዚህ ሕፃናት አእምሮአቸው በመጥፎ ወሲባዊ ፊልም ተመርዟል። አንዳንዶቹ ቤተሰቦቻቸው ያለባቸውን ዕዳ መክፈል ስላልቻሉ እንደ መያዣ ሆነዋል።

ከሰሜናዊ ኢጣሊያ ዝሙት አዳሪዎች ውስጥ 10 በመቶው ዕድሜያቸው ከ10-15 ዓመት ሲሆን፣ 30 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከ16-18 ዓመት የሚደርሱ ወጣቶች ናቸው።

በአገራችን ኢትዮጵያም ቢሆን ሁኔታዎቹ ከዚህ የከፋ እንጂ የተሻሉ አይደሉም። በ1987 ዓ.ም የተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት እንዳመለከተው ከኢትዮጵያ ሕዝብ 45%

የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ1-14 የሚደርስ ልጆች ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ ከቁጥራቸው ብዛት ትይዩ የእኛን ችግር ቀማሾች ናቸው።

«ልጅ በዕድሉ ያድጋል» በሚል ብሒል የታጠረው ለልጆች ተገቢ እንክብካቤን አያደርግም። የሥነ-ተዋልዶ ትምህርት እንደሚገባ ባለመስፋፋቱ የቤተሰብ አቅም ከልጆች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አይደለም። የአገራችን ሕዝብ በተደጋጋሚ የሚጋፈጠው ረሃብ፣ ጦርነትና ሌሎች አደጋዎች የመጀመሪያ በትራቸውን የሚያሳርፉት በልጆች ላይ ነው።

ከአንዳንድ አጠቃላይ መረጃዎች በመነሣት የልጆችን መከራ ልብ እንበል፡-

- ከኢትዮጵያ ሕዝብ 50% ያህሉ ከ16 ዓመት ዕድሜ በታች ነው።
- ይህ ማለት ወደ 30 ሚሊዮን የሚጠጉ ልጆችን እግዚአብሔር ለምድራችን ሰጥቷል።
- ጥናቶች እንደሚያመለክቱን ከ5 ዓመት በላይ ሳይቆዩ በጨቅላ ዕድሜያቸው የሚቀጠፉ ሕፃናት ከ1000 ውስጥ 226 ይሆናሉ።
- ሕክምና የሚያገኙት ሕፃናት ከ100 ውስጥ 46 ያህሉ ብቻ ናቸው።
- ከ100 ሺህ በላይ ሕፃናት የጎዳና ተዳዳሪ ሲሆኑ፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሃያ ሺህ የሚጠጉ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች እጅግ አስቸጋሪ ለሆነ ሕይወት ተጋልጠው ይገኛሉ።
- በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከ100 በላይ ሕፃናት በአንድ ክፍል ይማራሉ። ይህም ሆኖ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ የከተማ ልጆች የመማር ዕድል የላቸውም።

ሰቆቃው ብዙ ነው። ከዚህ አኳያ የልጆች የዛሬ አበባነት እውነት ቢሆንም፣ የነገ ፍሬነታቸው ያጠራጥራል። በዚህ ሁሉ አልፈው ግን አገርን እንዲረከቡና መጪውን ዘመን



እንዲዋጁ ይጠበቃሉ። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ልጆች ዛሬ ለአደጋ ተጋልጠዋል። ምን ይበጃል?

ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች እንደሆኑ እስክንጠግብ ሰምተናል። በጽንሰ አሳብ ደረጃ እውነት ነው። ግን አበባ ተገቢ እንክብካቤ ካላገኘ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል? በፍጹም!

የእኛዎቹ አበቦች ወደ የምንናፍቀው መልካም ፍሬ እንዲሸጋገሩ ፍቅር፣ ዋስትናና ሰላም ይሻሉ። ይህ ሁልጊዜ የሚያሳስበኝ ነገር ነው። አነስተኛይቱን ይህችን መጽሐፍ ከግብ ለማድረስ ሦስት ዓመት ተኩል ፈጅቶብኛል። ትንሽ የማይባሉ ኅትመቶችን አገላብጫለሁ። ከወላጆች፣ ከሕፃናት አገልጋዮችና አሳዳጊዎች፣ ከባለሙያዎችና ከራሳቸው ከባለ ጉዳዮቹ ጋር ተወያይቻለሁ።

በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ሪፖርተርና የገጾች አዘጋጅ ሆኜ ስሠራ ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር የተያያዙ በርካታ ቁም ነገሮችን መገንዘቤ አልቀረም። ይልቁንም በዕለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የእሑድ እትም ላይ «ስንበት ለልጆች» የሚለውን ዓምድ ከጀመሩት ሁለት ጋዜጠኞች አንዱ መሆኔ ግንዛቤዬን ከፍ ለማድረግ ረድቶኛል። ስለዚህ ታላቅ ዕድልም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ስለ ልጆች ባሰብኩ ቁጥር ወደ አእምሮዬ የሚመጣው አባባል «መውለድ ብቻ አይበቃም» የሚል ነው። ከእኛ ይልቅ የዘመኑን ክፋት የሚጨልጡት ልጆች ናቸው። ግራና ቀኛ ቸውን ለይተው በማያውቁበት ዘመን የሚከሰተውን ጦርነት፣ ረሃብ፣ ዐውሎ ነፋስ፣ ወዘተ. . . እንዴት ማምለጥ እንዳለባቸው ባለማወቅ ይረግፋሉ።

ዘመኑ ክፉ ነው፤ ጆሮ ደግ ነገርን አይሰማም። በዚህ ጊዜ ወደ ምድራችን ብቅ ያሉት የእኛ ልጆች አገርን የሚረከቡት በየት በኩል አልፈው ነው? እውን በሥነ- ምግባር የታነጹና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ተተኪዎችን ማፍራት ይቻላል?

አብላጫው ምላሽ «አይቻልም!» የሚል ይሆናል።

በእምነት ዓይን ግን ሌላ ምላሽ እናያለን። ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል! በእግዚአብሔር ስም የተጠሩ አገልጋዮች በመገናኛው ድንኳን ከልጃገረዶች ጋር ለመተኛት በደፈሩበት ዘመን ሳሙኤል የሚባል ታማኝ አገልጋይ ብቅ አላለምን? (1ኛ ሳሙኤል 2:22።) እንዲታዘዙ፣ ሰውንና እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ ታማኞች እንዲሆኑና ኃላፊነትን እንዲቀበሉ ልጆቻችንን ማስተማርና ማሠልጠን ይገባናል። አኗኗራችንም የዚሁ መገለጫ ነው። የሕይወት ምሳሌነትን ልጆች በጥንቃቄ ያስተውሉታልና።

ቤተሰብ ዛሬን ውሎ ለማደር በሚታገልበት አገር ልጆቻችንን ማሠልጠን ቀላል ተግባር አይደለም። ሆኖም፣ በምንም መንገድ ይህ ሊተገበር ያሻል።

ስለ ልጆች ማወቅ ጥቅሙ የትየለሌ ነው። ለምሳሌ፣ ከሁለት እስከ አራት ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉት ልጆች ከአምስት ደቂቃ በላይ በትዕግሥት ሊያደምጡ አይችሉም። ይህን የተረዳ ወላጅ እነርሱን ለማጫወት ሲል ረዥም ታሪክ ፍለጋ አይባዝንም። ደግሞም ቶሎ ይረሳሉ። ስለሆነም ሰኞ የተነገራቸው ነገር ረቡዕ ቢደገም ሰለቸን ብለው አያጉረመርሙም። እነዚህን ነገሮች ለማስታወስ ይህቺ ጥራዝ እንደምትጠቅም እምነቴ ነው።

«ድሮም አትረባም»፣ «ዓይንህ ይጥፋ»፣ «ባትወለድ ይሻልህ ነበር» በሚሉ የመርገም ዜማዎች አድገናል። ልጆቻችን ግን ተቃራኒው ሊሆንላቸው ይገባል። ልንባርክ ተጠርተናልና።

ልጆቻችን ገና በማኅፀን ሳሉ ጀምሮ የጸሎት ድጋፍ ይሻሉ፤ ዙሪያቸውን በምልጃ ካላጠርን በስተቀር ጭው ካለው የዓለም ባሕር ገብተው መስጠማቸው አይቀሬ ነው።

እግዚአብሔር ልጆች እንጂ የልጅ ልጆች የሉትም። ሁሉም (ልጆችን ጨምሮ) ኃጢአትን ስላደረጉ በክርስቶስ በኩል እርቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል (ሮሜ 3:23)።



አንድ እሑድ የአምልኮ ፕሮግራም ለመካፈል በአቅራቢያዬ ወደሚገኝ ጸሎት ቤት ሄድኩ፤ የደረስኩት ቀደም ብዬ ነበርና ዙሪያዬን የመመልከት ዕድል ነበረኝ። በዚህ ወቅት ነበር አንዲትን ልጅ ያየሁት። ዕድሜዋ ከ8-9 ዓመት ይደርሳል። ሲበዛም ቆንጆ ናት። አሳብ የያዛት ግን ትመስላለች።

«ጌታ ሆይ፣ ይህችን ልጅ ታያታለህ? ውበቷ ወጥመድ ነው። ደግሞም የክርስቲያን ቤተሰብ ልጅ ናትና ዲያብሎስ አይወዳትም። ታዲያ ይህን ክፉ ዘመን እንዴት ታልፋዋለች?» ስል ዓይኖቼን በመጨፈን የዝምታ ጥያቄ አቀረብኩ። ለጥቂት ደቂቃዎች ማዳመጥ ነበረብኝ። ግን በድንገት ዓይኖቼን ገልጬ ተመለከትኩ፤ እናም ያየሁት እጇን በአፏ ላይ የሚያስጭን ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ትጸልያለች፤ ጮርቃ ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል፤ ከፊትዋ የሚንቦገቦገው ብርሃን የውስጧን ሐሤት ለመረዳት አያስቸግርም።

በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀችው በዚያ ሰዓት ይሁን ከዚያ በፊት ለማጣራት ምቹ ጊዜ አላገኘሁም። ቢሆንም ጥያቄዬ ተመልሶልኛል። በሚገባኝ መንገድ «የዘላለም ሕይወት ያገኙና ሰማያዊውን ኃይል የተቀበሉ ልጆች በአምላካቸው ጸጋ እያለፉ ዘመናቸውን ለመዋጀት ይችላሉ» ብሎኛል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር፤ ሌላ መፍትሔ የለም።

ደኅንነት የግል ነው! እኛ መጋቢ፣ ወንጌላዊ፣ አስተማሪ፣ ነቢይ ወይም ሐዋርያ መሆናችን ለልጆቻችን መዳን ዋስትና አይሆንም። ልጆቻችን በቤተ ክርስቲያን ማደጋቸውም ለዘላለም ሕይወት አያበቃም። ጌታን ለመቀበል መወሰን አለባቸው (ዮሐ. 1:12)።

ዶክተር ኦስዋልድ ጄ. ስሚዝ፣ «እስከ ሩቅ ስፍራ የሚያሳይ ብርሃን ከቤት ውስጥ እጅግ ደምቆ ያበራል» ይሉ ነበር። እውነት ነው። ምስክርነታችን ወደ ዓለም ሁሉ የሚሰፋው ከመኖሪያ ስፍራችን ጀምሮ ነው።

የወንጌልን ቅብብሎሽ እኛም በሚገባ መወጣት

ይጠበቅብናል:: በዱላ ቅብብሎሽ ሩጫ ላይ ፈጣኑ ሰው የሚመደበው መጨረሻው ዙር ላይ ነው:: በጊዜና በተገቢው አኳኋን ካቀበልናቸው ልጆቻችን ከእኛም ይፈጥናሉ::

ስለ ኮካ ኮላ ጥቂት ሳትሰሙ አልቀራችሁም:: ሁሉ ሰው ይህን ስም እንደሚያውቅ እናስባለን:: ካምፓኒው ግን በየዓመቱ ለማስታወቂያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮችን ያወጣል:: ይህ ለምን አስፈለገ?

አንድ የካምፓኒው ባለሥልጣን ስለ ጉዳዩ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፣ «በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይሞታሉ፤ ስለሆነም የኮካ ኮላ ደንበኞነታቸው ይቆማል:: በአንጻሩ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይወለዳሉ:: ስለ ኮካ ኮላም ሰምተው አያውቁም:: ለእነርሱ ስለ ምርታችን እንነግራቸዋለን:: ስለሆነም ይህ የማስተዋወቅ ሥራ መቆሚያ የለውም::»

እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ለመላው ዓለም የምናስተዋውቀው አዳኝ አለን:: በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት ወደ ምድራችን ይመጣሉ:: ነገር ግን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ ስለ ተፈጸመው የማዳን ሥራ አያውቁም:: ስለዚህ ሊነገራቸው ይገባል:: ይህም ሥራ የሚቀጥል እንጂ የሚቋረጥ አይደለም::

በዚህች አነስተኛ ጥራዝ ይዤ የቀረብኩት አጭርና ግልጽ መመሪያን ነው:: ምናልባትም ወደፊት ተጨማሪ ነጥቦችን አክል ይሆናል:: ለዚህም የጸሎት ድጋፋችሁን የምጠይቀው በትሕትና ነው::

ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ የልጆች ጉዳይ ግድ የሚላቸው አስተማሪዎች፣ አማካሪዎች፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና ሌሎች ተቋማት ይህን መጽሐፍ ሊጠቀሙ ይችላሉ::



# 3

# ጥቂት ስለ ልጆች

ማግባትና ልጆችን መውለድ ብቻ አይበቃም:: መንከባከብና ማሳደግ ስብዕናንም መቅረጽ ይቀጥላል:: እንዲያውም ዓመታትን የሚፈጀው ክንዋኔ ይህኛው ነው::

በቅጡ ማጤን ከተቻለ የእያንዳንዱ ልጅ አፈጣጠር አስደናቂ ነው:: በፍትወተ - ሥጋ ግንኙነት ጊዜ አራት ሚሊዮን የሚደርሱ የወንድ ዘር ሕዋሦች ወደ ሴቲቱ እንቁላል ይጓዛሉ:: በሩጫቸው አንዱ ብቻ ያሸንፋል:: እናም ጽንስ ይፈጠራል::

- ከ12ኛው ቀን ጀምሮ ልቡ መምታት ይጀምራል::
- ከ43 ቀናት በኋላ የአእምሮው ግፊት ሊለካ ይችላል::
- ከስድስት ሳምንታት በኋላ እጆቹና እግሮቹን ሊያንቀሳቅስ ይችላል:: የዓይኑና የጆሮው ውስጠኛ ክፍሎች እንዲሁም ጉበትና ኩላሊቱ ያድጋሉ::
- ሰባተኛው ሳምንት ላይ ዓይኖቹ ከሞላ ጎደል ተሟልተው አድገው ይገኛሉ::
- በ9ኛው ሳምንት አውራ ጣቱን መጥባት ይማራል::
- ከ14-16 ሳምንት ጣቶቹና ጥፍሮቹ ተሟልተው ያድጋሉ::
- ከ16ኛው ሳምንት በኋላ ኩላሊቶቹ ቀጭን ሽንት ማስወጣት ይጀምራሉ::
- በ20ኛው ሳምንት ልጁ እንደሚገባ ስለሚንቀሳቀስ እናቱ ይህ ይሰማታል::

- ከ35 ሳምንታት በኋላ ወደ መጨረሻው የእድገት ወቅት ይሸጋገራል:: በየቀኑም 28 ግራም ክብደት ይጨምራል::

እነዚህን ነጥቦች ያነሣነው ስለ ልጆች የመወለድ ሂደት መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው:: በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ጠለቅ ያለ እውቀት ያስፈልገናል::

እንደ ዘ- ወርልድ - ቡክ ኦቭ ኢንሳይክሎፒዲያ ትርጓሜ ከሆነ ልጅ ከ18 ወራት እስከ 13 ዓመት ዕድሜ ያለ ነው:: የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የሥነ-ልቦና ምሑር የሆኑት ፕሮፌሰር ጄሮም ካጋን ደግሞ ልጅ ማለት ጉልምስና ደረጃ ያልደረሰ ማለት ነው፤ በዚህ መሠረት ይህ ክልል እስከ 20 ዓመት ዕድሜ ያሉትንም ይጨምራል ይላሉ::

ልጅነት የምንለው የዕድሜ ክልል በርከት ያሉ ዓመታትን ማለትም ከ2-12 ያካትታል::

በእድገት ሥነ-ልቦና (Development Psychology) ጥናት መሠረት የልጅነት ዘመን በ2 ተከፍሏል:: በዚሁም አተያይ የመጀመሪያው የልጅነት ዘመን ከ2-6 ዓመት ሲሆን፣ የመጨረሻው የልጅነት ዘመን ደግሞ ከ6-12 ዓመት ያለው ነው::

ጄ. ኦማር ቤከር የተባሉት ጸሐፊ ደግሞ የዕድሜ ልዩነቶችን እንዲህ መድበዋቸዋል:-

| | |
|---|---|
| ከልደት - 24 ወራት | - ጨቅላ |
| 2 እና 3 ዓመት | - ቅድመ-ትምህርት |
| 4 እና 5 ዓመት | - የመጀመሪያው የልጅነት ዘመን |
| ከ6- 8 ዓመት | - መካከለኛው የልጅነት ዘመን |
| ከ 9-11 | - ኋለኛው የልጅነት ዘመን |
| 12 እና 13 | - ቅድመ-ጉርምስና |
| ከ14- 17 | - መካከለኛ የጉርምስና ጊዜ |
| ከ18-34 | - ኋለኛው ጉርምስና እና ወጣት ጎልማሳ |
| ከ35-64 | - መካከለኛ ጎልማሳ |
| ከ65 ዓመት በላይ | - ኋለኛው ጉልምስና (ሽምግልና) |



ዕድሜ በጨመረ ቁጥር እድገት መታየቱም ይቀጥላል:: ይህም በአካል፣ በስሜት፣ በቋንቋ፣ በአእምሮና በማኅበራዊ ሕይወት ነው:: አንዱን እንኳን ለምሳሌ ወስደን ብናይ፣ በመጀመሪያው የልጅነት ዘመን ልጆች በየቀኑ በአማካይ ከ5-8 ቃላትን እንደሚማሩ በጥናት ተረጋግጧል:: በመጨረሻው የልጅነት ዘመን ግን ፈጠን ያለ የቋንቋ እድገት ያሳያሉ:: የሰዋሰውን ሕግ በጠበቀ መንገድ አሳባቸውን ይገልጣሉ:: እያደጉ በሄዱ መጠንም የሌሎችን ስሜት የመረዳት ብቃታቸው ይዳብራል::

## ዕድሜና ሥነ - ልቦና

ከልደት እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ባሉት ጨቅላ ሕፃናት እንጀምር:: የእነዚህ ልጆች አእምሮ እንደ ነጭ ወረቀት ነውና በላዩ ላይ ምን እንደምንጽፍ እንጠንቀቅ:: ምንም አያውቁም ማለት ስሕተት ነው፤ መማር የሚጀምሩት ከተወለዱባት ደቂቃ ጀምሮ ነውና::

በአንደኛ ዓመታቸው ክብደታቸውና ቁመታቸው በሦስት እጥፍ ይጨምራል:: ንቁ ተንቀሳቃሾች ናቸው:: በዚህ ጊዜ አንዳንድ ቃላትን ያውቃሉ:: በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ቀላል ዓረፍተ ነገሮችን ይገጣጥማሉ:: ግን ማገናዘብና ምክንያት መስጠት አይችሉም:: ብቻቸውን ይጫወታሉ፤ እንግዳ ሰዎችን ሊፈሩ ይችላሉ:: ወደ ለመዱት ይጠጋሉ::

ከሁለት እስከ አራት ዓመት ዕድሜ ያሉት ልጆች ደግሞ ንቁዎች ናቸው:: ግን ሚዛናቸውን መጠበቅ ይቸግራቸዋል:: ቢንተባተቡም እንኳ ይናገራሉ:: በሦስት ዓመታቸው መልበስና

ማውለቅ ይችላሉ:: ሁሉን መነካካት ይወዳሉ:: ዕቃዎችንም ይሰብራሉ::

በጥያቄ የተሞሉ ናቸው:: ከአምስት ደቂቃ በላይ ማድመጥ ባይችሉም፣ ብዙ ይጠይቃሉ:: ታሪክ ቢደጋገምም አይሰለቹም፤ ምክንያቱም ይረሳሉ:: በቀላሉ ያለቅሳሉ:: ድጋፍን የሚሹ ናቸው:: ከሌሎች ጋር መጫወትና ትላልቆችን መኮረጅ ያስደስታቸዋል::

ልጆች ስለ ራሳቸው መልካም አመለካከት የሚያዳብሩትና ነጻነትን የሚለማመዱበት ዕድሜ ከ4-5 ዓመት ክልል ውስጥ ያለው ነው:: በታላቆች ላይ አመኔታን ያሳድራሉ:: ሁሉንም ነገር ለራሳቸው ይፈልጋሉ:: በትናንሽ ነገሮች እንኳ ይደነቃሉ:: ሌላው ቢናደድ ግድ የላቸውም፤ አሁን የሚማሩትን በዕድሜ ዘመናቸው ሁሉ አይረሱም:: በፍጥነት ያድጋሉ፤ ጨዋሂዎች ናቸው:: ከ5-10 ደቂቃ በላይ በጸጥታ መቀመጥ አይችሉም:: ንቁ አእምሮ አላቸው:: ማካፈልንና ከሌሎች ጋር መሆንን የሚማሩበት ጊዜ ነው:: ጥልቅ ስሜቶች አሏቸው፤ በጣም ሲያዝኑ፣ ሲደሰቱ ወይም ሊቆዝሙ ይችላሉ::

ከ6-8 ዓመት የሚገኙት ልጆች ደግሞ ጀማሪዎች ይባላሉ:: ይህም ከቤት ውስጥ ሥልጠና ባሻገር የቀለም ትምህርትንም ስለሚጀምሩ ነው:: እነዚህ ልጆች ንቁዎችና ተጫዋቾች ናቸው:: ግን ቶሎ ይደክማሉ:: ቀላል ነገሮችን ማንበብና መጻፍ ይችላሉ:: ነገሮችን መሰብሰብ፣ መማርና መመርመር ይወዳሉ:: ስሜታቸው ቶሎ ይጎዳል:: ለሰዎች ያዝናሉ:: ስሜታቸውን መግለጥ ባይችሉም፣ ችግረኞችን መርዳት ደስ ያሰኛቸዋል::

አንደኛ ደረጃዎች ተብለው የሚጠሩትና ከ9-11 ዓመት ዕድሜ ያሉት ልጆች ከሚገባው በላይ ንቁዎች ናቸው:: ከ4-6ኛ ክፍል ሊማሩ ይችላሉ:: ለመማር ትልቅ ፍላጎት



አላቸው:: ከቤት ውጪ ጥሩ ሲሠሩ ሲችሉ፣ ድካምም አያውቃቸውም::

ትንሽ ነገር ይበቃቸዋል:: አስተሳሰባቸው ቀጥተኛ ነው፤ አስቸጋሪ ጥያቄዎችንም ያነሣሉ፤ ሲያድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉ ይናገራሉ:: ደፋሮች ናቸው:: መሳቅ ይፈልጋሉ:: ሲናደዱ ስለሚናገሩት ነገር አይጠነቀቁም፤ መታወቅና መመስገንን ይፈልጋሉ::

መንፈሳዊ ነገሮችን ለማወቅ ይጓጓሉ:: ጀግኖችንም ያደንቃሉ፤ እንደ እነርሱ ለመሆንም ይፈልጋሉ::

## ፍላጐት

የልጆች ፍላጎት ብዙ ነው:: ነገር ግን ሁሉም ልጆች በጋራ ቢያንስ ሰባት ፍላጎቶች እንዳሏቸው ምሁራን ይስማማሉ:: እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው:-

1. ተደማጭነት
2. ዋስትና
3. ተቀባይነት ማግኘት
4. መወደድ
5. መመስገን
6. በሥነ ሥርዓት ወይም በሥነ ምግባር መታነጽ
7. እግዚአብሔርን ማወቅ

### 1. ተደማጭነት የማግኘት ፍላጎት:-

ተደማጭነትን ማግኘት የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት ነው:: ሕፃኑ ስለ እርሱነቱ ጤናማ ግምት ኖሮት እንዲያድግ ከተፈለገ ተገቢ ዋጋ ያለው መሆኑ እንዲሰማው ማድረግ አለብን::

ሕፃኑ ችላ የሚባል ከሆነ ግን ማንነቱን ለማሳየት ዓመፀኛ ሊሆን ይችላል:: በየትኛውም ትምህርት ቤት የምታዩት በጥባጩ ልጅ እወቁኝ እዩኝ ማለቱ ነው:: ስለዚህ:-

ሀ. እያንዳንዱን በስሙ ጥሩት፤ ከእንግዶች ጋር አስተዋውቁት::

ለ. ሕፃኑ አንዳንድ ነገሮችን ለመረዳት ወይም ለማድረግ የሚችልበትን ዕድል ስጡት::

ሐ. በአንዳንድ ሁኔታዎች የማይሳካለትን ልጅ እንደገና እንዲሞክር አበረታቱት እንጂ በምንም አኳኋን አታንጓጥጡት ወይም አትቀልዱበት::

መ. ልጁን እንደምትተማመኑበት እንዲያውቅ አድርጉ:: ሰዎች ሲተማመኑብን ለራሳችን ያለን ግንዛቤ ይዳብራል:: በቤት ውስጥ አንዳንድ ኃላፊነት ከተሰጠው በጥባጭ የተባለው ልጅ እንኳን ሊስተካከል ይችላል::

ሠ. ስለሚያሳስቡአቸው ነገሮች ሲያወሩላችሁ በሙሉ ልብ አድምጡአቸው፤ ለዚሁ የተመቻቸና ልጆችን የምትረዱበት ጊዜ ይኑራችሁ::

## 2. ዋስትና የማግኘት ፍላጎት

ሕፃናት ስለ ራሳቸው ጤናማ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ዋስትና፣ ልበ ሙሉነትና መረጋጋት ሊኖራቸው የግድ ነው:: ይህ ዋስትና የማግኘት መሠረታዊ ፍላጎት ካልተሟላላቸው ግን ፈሪ ወይም ዓይናፋር ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህም ወደ ዓመፀኝነት ይመራቸዋል፤ የኋላ ኋላም እንዲህ ዓይነት ልጆች የአልኮል፣ የዕፅ እንዲሁም የሌሎች አጉል ልምዶች ተገዢ ይሆናሉ::

ልጆች ዋስትና እንዲኖራቸው እንዴት መርዳት ይቻላል?

ሀ. ደግ፣ የተረጋጋችሁና ፈገግተኛ ሁኑላቸው::



ለ. ምንም እንኳን በጥባጭ ቢሆኑና ኃላፊነታቸውን መወጣት ባይችሉም፣ ለሕፃናቱ ፍቅርና ትኩረትን አትንፈጓቸው::

ሐ. በቤትና በት/ቤት ሊኖራቸው ስለሚገባ ሥነ ምግባርና ደንብ አስረዷቸው፤ ሥርዓት ያለው አኗኗር የተረጋጋ አካባቢን ይፈጥራል፤ ለትናንሽ ልጆች ዋስትናን ይሰጣቸዋል::

መ. ለሕፃናት ፍቅርን አሳዩዋቸው፣ እቀፏቸው፣ ጉልበታችሁ ላይ አስቀምጧቸው:: ይህንን በማድረግ ዋስትና እንዲሰማቸው ልታደርጉ ትችላላችሁ:: ጌታ ኢየሱስ መልካም ምሳሌ ሰጥቶናል፤ ሕፃናቱን አቀፋቸው (ማር. 10-16)::

## 3. ተቀባይነት የማግኘት ፍላጎት

አንድን ሕፃን መቀበል ማለት እንደ ሰውነቱ ልጁን መውደድ መቻል ማለት ነው:: ሰዎች እንደ እርሱነቱ ሲቀበሉት እግዚአብሔርም እንደ ተቀበለው ይሰማዋል:: ሕፃኑ እንዳለ ከተቀበልነው እርሱም ሌሎችንም ሆነ ራሱን ይቀበላል::

አንድን ልጅ እንደ ተቀበልነው እንዲሰማው እንዴት መርዳት እንችላለን?

ሀ. ልጆች ሰው እንደ ሆኑ አድርጋችሁ ውደዷቸው::

ለ. አንዳንድ ቀለል ያሉ ነገሮችን እንዲሠሩ ዕድል ስጧቸው:: ሥራውን እንደሚገባ በመሥራታቸው ደስ እንዲሰኙ መንገድ ፍጠሩላቸው:: ማንኛውም ልጅ አንድ ነገር በማድረግ በሚገኘው ደስታ ተካፋይ እንዲሆን አድርጉ::

ሐ. ሕፃናት ሊነግሯችሁ የፈለጉትን የራሳቸውን ጉዳይ አድምጡአቸው::

መ. ሕፃናት መሆናቸውን አትዘንጉ፤ ስለዚህም እንደ አዋቂዎች ያለ ባሕርይ አትጠብቁባቸው::

ሠ. በጨዋነት አክብሮት አሳዩአቸው፤ በዚህ መንገድ እናንተንም ሆነ ሌሎችን ማክበር ይማራሉ።

## 4. የመወደድ ፍላጎት

ሌሎችን መውደድና በሌሎችም መወደድ ሁለት የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች ናቸው። ልጆች ከተወደዱ እነርሱም ሌሎቹን ይወዳሉ።

ፍቅር የልጆችን ልብ ዘልቆ ለመግባት ዓይነተኛ ቁልፍ ነው።

ልጆች እንደምንወዳቸው እንዲሰማቸው ማድረግ እንዴት ይቻላል?

ሀ. ከመኖሪያ ውጪ ከሕፃናት ጋር አብራችሁ የምታሳልፉትን ጊዜ አመቻቹ።

ለ. ልባችሁን ክፈቱላቸው።

ሐ. የሚያወሩላችሁን በፍላጎት አድምጡአቸው።

መ. ምንም ዓይነት ስጦታ ሲሰጧችሁ አድንቁላቸው።

ሠ. መልካሞቹንም ሆነ ክፉዎችን ስለሚወደው ሰማያዊ አባት ንገሯቸው (ሮሜ 5:8)።

ረ. ያለ አንዳች አድልዎ ሁሉንም ሕፃናት እኩል ውደዱ። ምንም ዓይነት ማበላለጥ እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ።

## 5. የመመስገን ፍላጎት

ይነስም ይብዛ እያንዳንዱ ሕፃን የሚመሰገንበት ነጥብ እንዳለው አትርሱ። ሕፃናትን ባመሰገናችኋቸው መጠን እነርሱም ይበልጥ ሊያስደስቱአችሁ ይሞክራሉ። ነቀፌታ ተቃራኒ ምላሽን ይፈጥራል። ልጅን ማበረታታትና ጎሽ ማለት ግን በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን በቀና ሁኔታ ለማደግ ይረዳዋል። ልጆች አንድ እውቀት ሲቀስሙ (ለምሳሌ፣



ብስክሌት መንዳት) ወይም ሥራ ሲያከናውኑ (ለምሳሌ፣ አልጋ ማንጠፍ) አድናቆትና ምስጋናን ይጠብቃሉ። በሰዎችም ፊት ቢሆን እንኳ ይህን ለማድረግ መሰሰት አያስፈልግም።

እንዴት በምስጋና ለልጆች ቀና አመለካከት ማስጨበጥ ይቻላል?

ሀ. መልካም ስለሆኑ ሳይሆን የአቅማቸውን ያህል ስለ ሠሩ ብቻ ሕፃናትን አመስግኑአቸው። ለምሳሌ፣ ወለሉን አጽድተው ከሆነ ጉድለት ብታዩበት እንኳን፣ «ጎሽ በጣም አሳምራችሁታል» በሉአቸው።

ለ. ባይሳካላቸው እንኳ፣ ስለ ሙከራቸው አመስግኑአቸው። ይህም እንደገና እንዲሞክሩ ያበረታታቸዋል።

ሐ. በራሳቸው ፈቃድ ተነሣስተው ለሚያደርጉት ነገር በሙሉ አመስግኑአቸው። ለምሳሌ፣ እናንተን አንዳንድ ሥራ በሚረዱበት ጊዜ ሊሆን ይችላል።

መ. ቀለል ያለ ስጦታን በመስጠት ሕፃናቱን አበረታቱአቸው።

## 6. በሥነ ሥርዓት ወይም በሥነ ምግባር የመታነጽ ፍላጎት

በሥነ ሥርዓት ወይም በሥነ ምግባር ያልታነጸ ልጅ ዋስትና አይሰማውም። ማንም የሚያስብለት ወይም ስለ እርሱ ደንታ ያለው አይመስለውም። ለሁሉም ነገር የተቀመጠውን ገደብ ማሳየት ግን እንደምንወደውና ዋስትና እንዲሰማው ያደርገዋል።

በቤትና ትምህርት ቤት ውስጥ ገደብ ማበጀት የሚቻለው እንዴት ነው?

ሀ. ጥራት ያለውና ግልጽ የሆነ ደንብ ይኑራችሁ፤ የምታወጧቸው ደንቦች ወይም የምትሰጧቸው መመሪያዎች በተቻለ መጠን ጥቂት ይሁኑ። እንዲከተሏቸውም ጠይቋቸው።

ለ. በሰዎች ወይም በጓደኞቻቸው ፊት አታዋርዷቸው፤ በጓደኛ ወይም በሰዎች ፊት የሚደረግ ቅጣት ውጤት የለውም::

ሐ. ቢያስፈልግ ቅጧቸው ወይም ይቅርታ አድርጉላቸው እንጂ አትዛቱባቸው፤ አታስፈራሯቸው::

መ. ሕፃናቱን ማበረታታት፣ ማመስገንና ጎሽ ማለት ከመቀለድና ከሚንጓጠጥ ይልቅ ይረዳቸዋል:: በልጆች ላይ በፍጹም አትቀልዱ::

## 7. እግዚአብሔርን የማወቅ ፍላጎት

ሕፃንም ይሁን አዋቂ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ይፈልጋል (መክብብ 3:11):: ብዙ ጊዜ ግን የሕፃናትን መንፈሳዊ ፍላጎት እንንቃለን:: ለሚያቀርቡት ጥያቄ መልስ አንሰጣቸውም፤ ወደ ጸሎት ስብሰባዎችና ወደ መሳሰሉት አንወስዳቸውም:: ይህ ግን ተገቢ አይደለም::

(ማስታወሻ:- ይህ ርእስ ጉዳይ «ልጆችን ወደ እውነት መምራት» በሚለው ምዕራፍ በስፋት ይብራራል::)



# 4

## መጪው ትውልድ

ሁለት ነገሮች ሊያስጨንቁን ይገባል:: አንደኛ፣ እንደ ማንኛውም ሰው ልጆቻችን ምርጫ አላቸው:: በዚህ መሠረት መንግሥተ ሰማያት መግባት ይችላሉ:: ካልፈለጉም ላላመኑት የተዘጋጀው መከራ ይቆያቸዋል:: ሌላው፣ የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን፣ ያውም ባለቀ ሰዓት ላይ ነው:: ይህ ዙሪያችንን ከሁሉ የከፋ ነገር የሚታይበት ያደርገዋል::

ሰይጣን አዲሱ ትውልድ መልካምን ነገር እንዲያይ አይወድም:: በተለይም እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልካም ነገርን ሊያደርግ ሲንቀሳቀስ የሰይጣን ምላሽና ሤራ በልጆች ላይ ያተኩራል:: ለዚህም ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል:: በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ለማውጣት ሲሰናዳ፣ ሰይጣን በንጉሡ ትእዛዝ ወንድ ልጆች ሁሉ እንደ ተወለዱ እንዲገደሉ አደረገ:: ሆኖም፣ ነፃ አውጪው መሪ ሙሴ በእግዚአብሔር ጥበብ አመለጠ (ዘፀ. 1:15):: ዓለምን በማዳን ዕቅዱ ጌታ ኢየሱስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ በሄሮድስ ትእዛዝ ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች እድሜ ያላቸው ሕፃናት ሁሉ ተገድለዋል:: እግዚአብሔር ግን በመልአኩ በኩል ተናግሮ የኢየሱስ ወላጆች ወደ ግብፅ እንዲሸሹ አደረገ (ማቴ. 2:16):: አሁንም የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት በሚጠብቀው በዚህ ትውልድ ላይ ሰይጣን ሤራ አለው:: ልጆችን ከዚያ እንዲያመልጡ በእግዚአብሔር ጥበብ ልንረዳቸው ይገባል::

እርሱን የሚያውቁ ልጆች እናሳድግ ዘንድ ከማንም ይልቅ እግዚአብሔርን ግድ ይለዋል:: ስለዚህም በትንቢተ ሚልክያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 15 «እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ

አንድ አድርጉ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን?» የሚል ቃል እናገኛለን::

አንዳንዶች እነርሱ መንፈሳዊ ስለሆኑ ብቻ ልጆቻቸውም እንደዚያ የሚሆኑ ይመስላቸዋል:: ይህ የተሳሳተ ግምት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው ብዙ ካህናትና የእግዚአብሔር ሰዎች «ምናምንቴ» የተባሉ ልጆችን አፍርተዋል (1ኛ ሳሙ. 2:12):: ስለዚህ መጠንቀቅ አለብን::

ብዙ ጊዜ እንደምናየው የመጀመሪያው ትውልድ ከእግዚአብሔር ጋር ጉዞ ከጀመረ፣ ሁለተኛው በበለጠ ኃይል ይከተላል:: ሦስተኛው ደግሞ በተቃራኒው መንገድ ይሄድና ታላቁን ኃላፊነት የሚዘነጋ ይሆናል:: ለዚህም ዳዊት፣ ሰለሞንና ሮብዓምን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል:: ይህ ሊስተካከል የሚገባው ነገር ነው:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ልጆች ገና ከሕፃንነታቸው ጌታን እንዲያውቁ በማድረግ ነው::

በአሜሪካ የሴሎ ክርስቲያኖች ኅብረት መጋቢ የሆኑት ጂየሪ ኩክ *መጪው ትውልድ ይመራ ዘንድ ኃይልን ማስታጠቅ* በሚል ርእስ ስለ እረኞች አወጣጥ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሰጡት ትምህርት ላይ የመዋለድን ሕግ በአጭሩ እንዲህ አስቀምጠውታል:-

በፍጥረታትና በሰዎች ዘንድ አንዱ ዘር የራሱን ዓይነት ይወልዳል:: ተዋጊው ዳዊት እንደ እርሱ ያሉ ጦረኞችን አፍርቷል:: ሙሴ ኢያሱን፣ ኤልያስ ኤልሳዕን፣ ጳውሎስም ጢሞቴዎስን ተከተዋል:: ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን (ኋላም ሐዋርያት) ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንዲሰብኩ ልኮአል::

ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ እንድታበቅል ያደረገ፣ የሰውንም ልጆች እንዲበዙ ብሎም ምድርን እንዲሞሉአት የተናገረ እግዚአብሔር ነው (ዘፍጥ. 1:28)::



መውለድ ብቻ ግን አይበቃም፤ ማሳደግም ሙሉ አይደለም:: በተለይ የዘላለም ሕይወት ምሥጢር የተገለጠለት ቤተሰብ ግቡ ከነልጆቹ መንግሥተ ሰማይ መገኘት መሆን አለበት::

ሕዝባችንን በወንጌል መድረስ ከቻልን ታሪክ ይቀየራል:: መጪው ትውልድ ጌታን የሚያውቅ ይሆናል:: ትውልድን መቀየር ታሪክን መለወጥ ነው:: በሌሎች አገሮች የሆነው እዚህም የማይከናወንበት ምክንያት የለም::

ዶክተር ፖት ሞርጋን የተሰኙች አንዲት ሴት ስለዚሁ ስትናገር፣ «የአገርህን ታሪክ መቀየር የምትመለከተው በ3ኛው ትውልድ ላይ ነው» ብላለች:: እርሷ ወደዚህ አገልግሎት ስትሰማራ ፍሬው የሚደርሰው ለልጅ ልጆቿ እንደ ሆነ ስሌቱ ያመለክታል::

ሁለት ታሪካዊ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፤ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሺህ ዓመት ቆይቶ የዳኒሽ (ዴንማርክ) ወራሪዎች አንዲትን ደሴት በወረራ ያዙ:: በዚያም ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ጥቂት ሰዎችን አገኙ:: በእነርሱ በጣም ከመናደዳቸው የተነሣ ኃይለኛ ሥራ ሊሰጡአቸው ወሰኑ:: ያም ልጆችን እንዲጠብቁ ማድረግ ነበር:: ግን አልሰመረላቸውም፤ እነዚያ ክርስቲያኖች ልጆቹን ማንበብና መጻፍ ብቻ ሳይሆን፣ የእውነትንም ቃል አስተማሯቸው:: ከሦስት ትውልድ በኋላ የተመረጠው የደሴቲቱ ኘሬዚዳንት ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ነበር::

ደቡብ ኮርያንም እናንሣ፤ 25% የሚሆነው ሕዝቧ የዘላለምን ሕይወት ያገኘ ክርስቲያን ነው:: ከ150 ዓመታት በፊት የጀርመንና እንግሊዝ የወንጌል መልእክተኞች (ሚስዮናውያን) ወደዚያ ሄደው ነበር:: ትኩረት ያደረጉት በወጣቶችና በሕፃናት ላይ ሲሆን፣ በተለይም ለድሆቹ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት በቃሉ አሳደጓቸው:: ዛሬ በዚያ

ዘመን አገራቱን ወርሶ የነበረው ቡድሂዝም ስፍራውን ለክርስትና እየለቀቀ ነው::

ትውልድን ማስተማርና መቅረጽ ምን ያህል ወሳኝ እንደ ሆነ ብዙዎች መስክረዋል:: ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ «ለክርስትና እምነት ሕፃናትን ቸል እንደ ማለት ያለ ትልቅ ስንፍና የለውም፤ ስለዚህ እምነታችን ተመልሶ በሁለት እግሩ እንዲቆም ብትሹ ሥራውን ከእነርሱ ጀምሩ» ብሏል:: አንድ የአይሁድ መምህር ደግሞ፣ «እስራኤል እስካሁን የመኖሯን ምሥጢር ማወቅ ትፈልጋላችሁን? ልጆች የቀደመውን ታሪክ በሚገባ ስለሚማሩ ነው:: ያመነ አይሁድ ሃይማኖታዊ ነገሮችን ለልጆቹ ከማስተማር አይቦዝንም» ብሏል:: የሜተዲዝም መሥራች የሚባለው ታላቁ የመነቃቃት ሰባኪ ጆን ዌስሊ ደግሞ፣ «ይህ መነቃቃት እንዳይቆም ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ ልጆቻችሁን አስተምሯቸው» በማለት ተናግሯል::

ልጆችን በሸክላ፣ በደረቅ ስፖንጅና በአዲስ ሻማ መስለን ልናያቸው እንችላለን:: እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር እጅ እንደ ሸክላ እንደ ሆንን የጌታ ቃል ይናገራል:: እናም ሕፃናት ደግሞ በአደራ የተሰጡን ናቸው:: እንደሚገባ ልንቀርጻቸው ያስፈልጋል:: የሚሄዱበትን መንገድ በቅጡ ካሳየናቸው ሲያድጉ ከዚያ አያፈነግጡም (ምሳሌ 22:6)::

ልጆች ስለ ሕይወት፣ ስለ ሰዎችና ስለ እግዚአብሔር የሚያስቡትን ሁሉ በአብዛኛው የሚያገኙት በትንሽነታቸው ነው:: እንደ ሸክላ ናቸውና በውስጣቸው ምን እንደምናኖር ማወቅ ይገባናል::

ልጆች ታላላቆችን ያምናሉ:: የሚኖሩበትን ዓለምና አካባቢያቸውን ለማወቅ በጣም ይጓጓሉ፤ ከዚህ አኳያ በደረቅ ስፖንጅ ልንመስላቸው እንችላለን፤ ወደ ንጹሕ ውኃ ብትወስዱት ይመጠጠዋል:: ቆሻሻ ውስጥ ብትጥሉትም እንዲሁ፤ ስለዚህ መልካሙን እናስጨብጣቸው::



ወደ ጌታ የሚመጣ ጎልማሳ ግማሽ ዕድሜውን አባክኗል፤ ሕፃኑ ግን ዘመኑ ሁሉ ከፊቱ አለ፤ ከዚህ የተነሣ ሕፃኑ በሙሉ ሻማ ሊመሰል ይችላል:: አንድን ጎልማሳ ማዳን አንድ ነፍስ ማዳን ሲሆን፣ አንድን ሕፃን ወደ ጌታ ማምጣት ግን ነፍስ እና ዕድሜንም ጭምር መማረክ ነው:: በአሁኑ ሰዓት በምድራችን ካሉ እና ዳግም ከተወለዱ ክርስቲያኖች 85% የሚሆኑት ይህን ውሳኔ ያደረጉት ከ4-14 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ሳሉ እንደ ሆነ ይታመናል::

«የምኖረው ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክና ለዘላለማዊነት ነው:: ስለሆነም አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እፈልጋለሁ» በማለት አዘውትሮ ይናገር የነበረው አሜሪካዊ የወንጌል ሰው ዲ. ኤል. ሙዲ ከዕለታት በአንዱ ቀን ከምሽት አገልግሎት ዘግይቶ ወደ ቤት ይመለሳል:: ሙዲ ወደ መኝታው ሲወጣ በቀስታ ቢያደርገውም እንኳ ሚስትየዋ ከእንቅልፍ መንቃቷ አልቀረም:: በእንቅልፍ ልቧም፣ «የምሽቱ አገልግሎት እንዴት ነበር?» ስትል ጠየቀችው::

«ድንቅ! ሁለት ተኩል ነፍሳት ዳኑ» በማለት መለሰ ሙዲ::

«መልካም ሆነ፤ ሕፃኑስንት ዓመቱ ነው?» አለች ወ/ሮ ሙዲ የቁጥሩ ምሥጢር እንደ ገባት ለማሳወቅ ፈገግ ብላ:: «አልተረዳሽኝም ሁለት ሕፃናት እና አንድ አዋቂ ነበሩ፤ የእነርሱ ሙሉ እድሜ በፊታቸው ያለ ሲሆን፣ ትልቁ ሰው ግን ዘመኑን አጋምሷል:: ለዚህ ነው ግማሽ ያልኩት» አለ ሙዲ::

ኤድዋርድ ኪምባል የተባለው የእሑድ ትምህርት ቤት አስተማሪ ለልጆች ታላቅ ፍቅር ነበረው:: በትርፍ ጊዜው እንኳ ወደ የቤታቸው በመሄድ ከመጎብኘት አይታቀብም:: ታዲያ አንድ ቀን ድዋይት. ኤል. ሙዲ የተባለውን ልጅ ወደ ጌታ ማምጣት ቻለ:: ሙዲም አድጎ ወንጌላዊ ሆነና እርሱ

በዳነ በ21 ዓመቱ ኤፍ. ቢ. ሜየርን ለክርስቶስ ማረከ:: ሜየር ጥሩ ሰባኪ ብቻ ሳይሆን ኀብኚም ወጣው፤ በዚህም ጄ. ደብሊው. ቻፕማንን ከጌታ ጋር ሊያስተዋውቀው በቃ:: ቻፕማን በወንጌል አገልግሎት ዘመኑ ለታዋቂው የቤዝ ቦል ተጫዋች ቢሊ ሳንዴይ የደኅንነትን ዜና ማድረስ ቻለ፤ ቢሊ ሳንዴይ ስፖርተኝነቱን ሳይተው ስብከቱን ቀጠለና በሰሜናዊ ካሮሊና ታላቅ የመነቃቃት ፕሮግራም አካሄደ:: በዚያው ወቅት ሞርዴካይ ሀም ሲሰብክ ቢሊ ግርሃም እጆቹን አንሥቶ ጌታን ተቀበለ፤ ቅብብሎሹ ዛሬም አልቆመም::



# 5

## ስለ እነርሱ መጸለይ

አባት ሆይ፣ ጸሎታችንን ስማ:: የልባችንን ቃላት አድምጥ፤ ስለ ልጆች እንዲህ እንጸልያለን:: ከክፉው ጠብቃቸው :: ከተሰወረ ወጥመድም አድናቸው:: ጨምድዶ ከሚያስቀርና እንደ አሸዋ ከሚያሰጥም ነገር ሰውራቸው:: ከዓለም ባዶ ደስታ፣ ካለማመንም ከሚመጣ ኃዘን አርቃቸው:: በሕይወት ምሬት እንዳይያዙ እርዳቸው:: በመራራ ውጊያ መካከል ደስ አሰኛቸው፤ የመሻታችንን ጩኸት ስማ:: ያለቃላት የምንነግርህንም አስብ:: እባክህ ልጆቻችንን ተመልከታቸው:: ወደ ቤትህም አስገባቸው::

* * *

ገንዘብ ሊገዛው የማይችለውን ውድ ስጦታ ለልጆቻችሁ ልትሰጡአቸው ትፈልጋላችሁ? በቂ ጊዜ ወስዳችሁ ጸልዩላቸው:: ይህን ብታደርጉ እናንተና ልጆቻችሁ የጸሎትን በረከት ለሁልጊዜ ትለማመዱታላችሁ:: ለልጆች መጸለይ ያለብን ከመቼ ጀምሮ ነው የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል:: በማኅፀን ሳሉ ብንጀምር ይመረጣል::

ለልጆች በምን ርእስ ላይ እንጸልይላቸው? እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው ወይስ ሌላ? በክርስቲያን ሥነ ምግባር እንዲታነጹና የመንፈስ ፍሬ በሕይወታቸው እንዲታይ ቢሆንስ? ጥሪያቸው ምን እንደ ሆነና የመጪ ጊዜ ሕይወታቸውን በተመለከተ ልንጸልይላቸው ብንሞክርስ? በወሩ 30 ቀናት ውስጥ አንድ አንድ ጉልህ ርእሶችን ይዘው በመጸለይና በመጨረሻው ቀን በመጠቅለል በልጆቻቸው ሕይወት ታላቅ ለውጥን እንዳዩ የሚናገሩ ወላጆች አሉ::

በዚህ አገባብ ለልጆቻችን እንጸልይ ዘንድ የሚደግፉን

በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች አሉን:: እስኪ ለምሳሌ ከዚህ በታች የቀረበውን የ30 ቀን የጸሎት ሠንጠረዥ እንመልከት:: በዚሁ ላይ ተመርኩዘም የራስን ፕሮግራም ማዘጋጀት ይቻላል::

1. ደኅንነት:- «ጌታ ሆይ፣ ለልጆቼ የጽድቅን ዝናብ አዝንብላቸው:: ስለዚህም እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር ያግኙ» (ኢሳ. 45:8፤ 2ኛ ጢሞ. 2:10)::
2. በጸጋና በእውቀት ማደግ:- «ልጆቼ የዓለም አዳኝና ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እውቀት እንዲያድጉ እጸልያለሁ» (2ኛ ጴጥ. 3:18)::
3. ፍቅር:- «በውስጣቸው ከሚኖረው የአንተ መንፈስ የተነሣ ልጆቼ የፍቅርን ሕይወት ይማሩ ጌታ ሆይ» (ኤፌ. 5:2)::
4. ቅንነትና የውሃት:- «የውሃትና ቅንነት እንዲጠብቋቸውና መለያቸው እንዲሆኑም ጭምር. . .» [መዝ. 24(25):21]::
5. ራስን መግዛት:- «አባት ሆይ፣ ልጆቼ በዙሪያቸው እንዳሉ እንደ ብዙዎች አይሁኑ:: ነገር ግን ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ እርዳቸው» (2ኛ ጴጥ. 1:6)::
6. የቃሉ ፍቅር:- «ልጆቼ ቃልህ ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ እንደሚወደድ፣ ከማርና ከማር ወለላም እንደሚጣፍጥ በማወቅ ያድጉ ዘንድ. . .» [መዝ. 18(19):10]::
7. ጽድቅ:- «እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ጻድቅ እንደሆንክና ጽድቅንም እንደምትወድድ፣ ልጆቼ የሚያደርጉትን ሁሉ በጽድቅ እንዲያደርጉ እርዳቸው» [መዝ. 10(11):7፤ ሚክ. 6: 8]::
8. አክብሮት:- «አባት ሆይ፣ ቃልህ እንደሚል ልጆቼ ለሁሉም ተገቢውን አክብሮት እንዲያሳዩ እርዳቸው» (1ኛ ጴጥ. 2:17)::



9. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት:- «ለእግዚአብሔር መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ መፈጠራቸውን በማሰብ ለራሳቸው መልካሙን አመለካከት እንዲያዳብሩ እርዳቸው» (ኤፌ. 2:10)::
10. ታማኝነት:- «ታማኝነት ከልጆቼ አይራቅ፤ አደራን መቀበል ይችሉ ዘንድ» (2ኛ ጢሞ. 2:2)::
11. ጽናት:- «ልጆቼ በባሕሪያቸውና በሥራቸው ሁሉ ሁልጊዜ ጠንካራና የጸኑ ይሁኑ» (ዘዳግ. 31:6)::
12. ንጽሕና:- «ንጹሕ ልብን ለልጆቼ ፍጠር፤ ያ የልብ ንጽሕና ደግሞ በሥራቸው ሁሉ ይገለጥ» [መዝ. 50(51):10]::
13. መልካምን ማድረግ:- «ጌታ ሆይ፣ ልጆቼ እርስ በርሳቸው መልካም ለማድረግ እንዲተጉ እርዳቸው» (1ኛ ተሰ. 5:15)::
14. ማካፈል:- «ልጆቼ እንዲረዱና እንዲያካፍሉ እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እንዲሰበስቡ . . . » [1ኛ ጢሞ. 6:18-19]::
15. ሰላም ወዳድነት:- «አባት ሆይ፣ ልጆቼ ወደ ሰላም ለመድረስ ማናቸውንም ዋጋ ይክፈሉ» (ሮሜ 14:19)::
16. ደስታ:- «ከመንፈስ ቅዱስ በሆነው ደስታ ልጆቼ ይሞሉ ዘንድ እጸልያለሁ» (1ኛ ተሰ. 1:6)::
17. ትዕግሥት:- «ጌታ ሆይ፣ ልጆቼ በሚሠሩት ሁሉ ትዕግሥት ይኖራቸው ዘንድ አስተምራቸው፤ በፊታቸው ያለውንም ሩጫ በትዕግሥት እንዲሮጡ እርዳቸው» (ዕብ. 12:1)::
18. ትሕትና:- «እግዚአብሔር ሆይ፣ ለሁሉም ትሕትናን ያሳዩ ዘንድ ይህን ችሎታ በልጆቼ ውስጥ አሳድግ» (1ኛ ጴጥ. 3:8)::

19. ርኅራኄ:- «ልጆቼ ርኅሩኅ እንዲሆኑ እርዳቸው» (1ኛ ዮሐ. 3:17)::

20. ኃላፊነት:- «ልጆቹ ኃላፊነት ስለ መውሰድ ያስቡ:: እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ይሸከም ዘንድ» (ገላ. 6:5)::

21. መርካት:- «ጌታ ሆይ፣ የምንኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ለልጆቼ አስተምራቸው» (ፊልጵ. 4:13)::

22. እምነት:- «ተስፋ የሚያደርጉትን ይወርሱ ዘንድ እምነት በልባቸው ውስጥ ሥር ይሰድድና ያድግ ዘንድ ስለ ልጆቼ እጸልያለሁ» (ዕብ. 11:1-40)::

23. መታዘዝ:- «እግዚአብሔር ሆይ፣ የታዛዥነት ልብ ኖሯቸው ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደሚገዙ እንዲያደርጉት እባክህ ልጆቼን እርዳቸው» (ኤፌ. 6:5)::

24. ተስፋ:- «የተስፋ አምላክ ልጆቼን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንዲበዙ አድርግ» (ሮሜ 15:13)::

25. ትጋት:- «ጌታ ሆይ፣ ልጆቼ ሥራን እንዲያከብሩና ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደሚያደርጉት ሁሉ በትጋት እንዲያደርጉ አስተምራቸው» (ቆላ. 3:23)::

26. በጎነት:- «ጌታ ሆይ፣ ልጆቼ በእምነታቸው ላይ በጎነትን እንዲጨምሩ እርዳቸው» (2ኛ ጴጥ. 1:5)::

27. ጥበብ:- «አባት ሆይ፣ ልጆቼ ጽድቅንና ፍርድን ቅንነትንም ይቀበሉ ዘንድ የሚያስችል ጥበብን የሚሰማ ሕይወት እንዲኖራቸው እጸልያለሁ» (ምሳ. 1:3)::

28. የጸሎት ሕይወት:- «የልጆቼ ሕይወት በጸሎተኝነት እንዲሞላና በየትኛውም ሁኔታ ማንኛውንም ጸሎት ሲያቀርቡና ሲለምኑ በመንፈስ እንዲጸልዩ እንዲተጉም አድርግ ጌታ ሆይ» (ኤፌ. 6:18)::

29. ምስጋና:- «ምስጋና የሚበዛለት ሕይወት እንዲኖሩና ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም



አምላካችንንና አባታችንን እንዲያመሰግኑ. . .» (ኤፌ. 5:20፤ ቆላ. 2:7)::

30. ምስክርነት:- «ክብርህን ለአሕዛብ ተአምራትህንም ለወገኖች ሁሉ ይነገሩ ዘንድ ይህን ስሜት በውስጣቸው አሳድግ» [መዝ. 95(96):3]::

## ለልጆች ለመጸለይ ስምንት ነጥቦች

እነዚህ ስምንት ነጥቦች ስለ ልጆች ስንጸልይ የሚጠቅሙን ናቸው:: የእነርሱ ዕድሜ ማነስና መብዛት ተጽዕኖ የለውም::

ሀ. የምትጸልዩላቸው መሆኑን ንገሯቸው:- ወላጆቻቸው ስለ እነርሱ እንደሚጸልዩ የሚያውቁ ልጆች እያንዳንዱን ዕለትና የትኛውንም ችግር የሚጋፈጡት በድፍረት ነው:: ያሉበትን ሁኔታ ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያውቅ እርግጠኞች ናቸውና::

ለ. ጥያቄያቸውን ተቀበሉ:- የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ጠይቁና በማስታወሻ ያዙ:: የበለጠ አንገብጋቢ የሆነውንም ምልክት አድርጉበት:: በዚህም ልጆች ምን ያህል ስለ እነርሱ ግድ እንደሚላችሁ ወደ እግዚአብሔርም እንደምታቀርቡዋቸው ያዩበታል::

ሐ. ከእግዚአብሔር ምሪት ጠይቁ:- ልጆቻችሁ ብዙ የጸሎት ጥያቄ ቢኖራቸውም ጉዳዩ እነርሱ ባዩት አቅጣጫ የሚሄድ ላይሆን ይችላል:: የችግራቸው መንሥኤ ምን እንደ ሆነ ትረዱ ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጣችሁ ለምኑት:: የራሳችሁን ምኞትም ሆነ የልጆቻችሁን ሕይወት ለእርሱ በአደራ አስረክቡ:: እርሱ ችግሮችን በራሱ መንገድ እንዲፈታና በጎ ምላሽን እንዲሰጥ ጸልዩ::

መ. በቀን በተወሰነ ሰዓት ጸልዩላቸው:- ልጆቻችሁ በሚፈልጉና በሚጠይቁትም መሠረት መጸለይ አንድ ነገር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በቀን ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ስለ

ልጆቻችሁ ጸልዩ:: ይህ ቋሚነት ያለው ልምምድ ይሆናችኋል::

ሠ. እንደ ጥያቄአቸው በማንኛውም ጊዜ ጸልዩ:- ልጆች እንቅፋት ገጥሟቸው ሊመጡ ወይም ጥሪ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ ተጨንቀው ስልክ ይደውሉላችሁ ይሆናል:: በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ያለቀጠሮ ለጉዳዩ ቅድሚያ በመስጠት ወዲያውኑ ጸልዩላቸው:: በአስቸጋሪ ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ለልጆች መልካም ነው::

ረ. በጋራ ጉዳዮች ላይ ጸልዩ:- ሁልጊዜ የጸሎት ጥያቄ ላያቀርቡ ይችላሉ:: በእንዲህ ዓይነት ጊዜያት 2 ወይም 3 ያህል የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሣት ልትጸልዩ ትችላላችሁ:: ለምሳሌም የሚከተሉትን ተመልከቱ:: ሌላም መጨመር ይቻላል (የእግዚአብሔር ጥበቃ፣ ጤንነት፣ መልካም ዝምድና፣ ክርስቲያናዊ ጓደኝነት፣ ምሪትና ውሳኔን ማድረግ፣ ችግርን መቋቋም፣ መልካም ዕይታ፣ ክንውን፣ በዕውቀት መብሰል፣ ግቦችና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ በረከት፣ መንፈሳዊ እድገት፣ በጌታና በራስ መተማመን፣ ደስታ፣ መለየት፣ ወዘተ. . .)

ሰ. የጸሎት ርእሶችን በሚገባ መዝግቡ:- ከላይ የተጠቀሱትን የጋራ ርእሶች በመንተራስ ለእያንዳንዱ ልጅ የምትጸልዩበትን ጉዳይ በተዘጋጀ ማስታወሻ መዝግቡ:: እንዲሆን የምትፈልጉትንም በዝርዝር ጽፋችሁ በእያንዳንዱ ልጅ መጽሐፍ ወይም ደብተር ውስጥ አኑሩት:: ይህ ጥሩ መበረታታትም ይሆናል::

ሸ. የተዘነጋውን እንዲያሳያችሁ ጌታን ጠይቁት:- በጣም ጥሩ የሚመስለው ጸሎት እንኳን አንዳንዴ የሰው ቅንብር ሆኖ ይገኛል:: ይህ ግን ሊስተካከል የሚችል ነው:: ስለሚጸለይበት ነገር ጊዜ ወስዶ ማሰላሰል አንዱ መፍትሔ ሊሆን ይችላል:: እግዚአብሔርን መጠየቅ ደግሞ ከሁሉ የተሻለ ነው::



# የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት በመጸለይና በማስተማር የታወቁት ኢትዮጵያዊው መጋቢ ሰይፉ ከበደ ለሕፃናት ይህ እንደሚያስፈልጋቸው አበክረው ይናገራሉ::

«ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ:: ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ» (ኢዩኤል 2:28)::

በኢትዮጵያ ጉባዔ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ያዕቆብ የተባለ የአራት ዓመት ሕፃን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ በልሳኖች ሲናገር አይተናል:: እንዲያውም ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልግ ጠይቀውት «ወንጌላዊ» ሲል መልሷል::

ለመጀመሪያ ጊዜ ሕፃናት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ባዩ ጊዜ ግራ ገብቷቸው ጌታን እንደ ጠየቁትና እርሱም እንደ ተናገራቸው መጋቢ ሰይፉ በአንድ መድረክ ተናግረው ነበር:: «በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ነው ቃሌ የሚለው» ነበር ያላቸው::

እስካሙኑ ድረስ ለሁሉም ክርስቲያን የተሰጠው ተስፋ እንደሚደርሳቸው ግልጽ ነው:: አብ የሚልከው የእውነት መንፈስም ያርፍባቸዋል::

* * *

«በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሻል?»

«አዎን ተሞልቻለሁ፤ ኢየሱስ ጌታ ነው!»

ብላቴና የተሰኘውና በኮምፓሽን ኢትዮጵያ ተጠባባቂነት የሚዘጋጀው መጽሔት የሕፃናት ድምፅ በሚለው አምዱ ሥር ካነጋገራቸው ሦስት ልጆች አንዷ የሰጠችው ምላሽ ነበር::

ራሔል ሡልጣን የሰባት ዓመት ልጅ ነች። ጌታን ከተቀበለች (በዚያ ወቅት) ገና ስምንት ወሯ ሲሆን፣ በደብረ ዘይት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንም የጥምቀት ሥርዓቷን ፈጽማለች።

ሚስ ሚጃሚ ይሌኒየስ ደግሞ በእሑድ የሕፃናት ትምህርት ቤትና በሌሎችም ተቀራራቢ መስኮች ከ25 ዓመታት በላይ አገልግለዋል። በርካታ የአፍሪካና የእስያ እንዲሁም የአውሮፓ አገሮችን ተዘዋውረው አገልጋዮችን ያሠለጠኑት እኚሁ የፊንላንድ ወይዘሮ በአንድ ወቅት ስለዚሁ ርእሰ ጉዳይ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እነሆ:-

- ሕፃናት መንፈስ ቅዱስ ሊሞሉ ይችላሉን?
- የዚህ መልስ አጭር ነው። አዎን፤ ሕፃናት በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ። ይህ በማንኛውም ጊዜ በዓይናችን አይተን ልናረጋግጠው የምንችለው ጉዳይ ነው። የእኛ የትልልቆች ችግር በእነርሱ የተሟላ ስብዕና ያለማመን ይመስለኛል። ሕፃናት ቅንና ቀጥተኛ ከመሆናቸውም በላይ ለጌታ እንደ ሙሉ ሰው ናቸው። ወንጌል ተሰብኮላቸው የመዳንን መንገድ ከተረዱ መንፈስ ቅዱስን ሊቀበሉ ይችላሉ። ጌታ መንፈሱን በዕድሜ ወስኖ አይሰጥም። ይህ በቃሉ ማስረጃነት የተረጋገጠ ነው። የሚሞላቸው ጌታ ቢሆንም፣ እኛ ደግሞ ልናዘጋጃቸው ይገባል።

## ልጆችን መባረክ

«በዚያን ጊዜ እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ. . . እጁንም ጫነባቸውና ከዚያ ሄደ» (ማቴ. 19:13-14)።

ቤተሰብን በተመለከተ የሥልጣን ተዋረድ ተበጅቷል። ከአብ ወደ ክርስቶስ፣ ከዚያ የቤቱ ራስ ወደሆነው አባት ተዘርግቷል። ይህ ሥልጣን የበታቾችን ለመቆጣጠርና



ለመቅጣት ብቻ ሳይሆን በመልካም የሚያገለግሉትን ለመሾምና ለመባረክ ነው።

በእግዚአብሔር ፈቃድ የተጋቡ፣ እርሱን ለመታዘዝ የሚወዱና ይባርካቸው ዘንድ ወደ ኢየሱስ የሚያመጡ ወላጆች ያሉአቸው ልጆች ምንኛ የታደሉ ናቸው?

በማቴ. 19:14 የተጠቀሱት ወላጆች የዚህ ዓይነቶች ነበሩ። እጁን ይጭንባቸውና ይጸልይላቸው ዘንድ ልጆችን ወደ ኢየሱስ አመጡ። እርሱም ሕፃናቱን ባረካቸው።

ለመሆኑ በረከት ስንል ምን ማለታችን ነው? መባረክስ? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ማብራሪያ ከሆነ ሰው ወይም ማንኛውም ነገር እንዲበዛ (ዘፍጥ. 1:22)፣ ወይም ጠቃሚ እንዲሆን (1ኛ ቆሮ. 10:16)፣ እንዲሁም መልካም ነገር እንዲያገኝ መመረቅ በረከት ይባላል። መባረክ ድርጊቱ ነው።

ልጆችን መባረክ ክህነታዊ ሥራ ነው። እነርሱም አብዝተው ይፈልጉታል። ይወዱታልም። የመጪውን ትውልድ ታሪክ የምንቀይረው በመባረክ እንጂ በሌላ አይደለም።

«አንድ ጊዜ ለአገልግሎት ስዘጋጅ ሳለ ጌታ ‹ልጆችን ባገኘሻቸው ቁጥር ባርኪያቸው› አለኝ» የምትለው ጀርመናዊቷ ዓለም አቀፍ የሕፃናት አገልጋይ አውክዬ መይኔማ ካጋጠሟት አንዱን እንዲህ ታስታውሰዋለች።

«አንድ ጊዜ በአንዲት የጀርመን ከተማ ስለዚሁ ካስተማርን በኋላ በረከትን የሚፈልጉ ወደፊት እንዲመጡ ጠየቅሁ። ዓይኔም በአንድ ወጣት ልጅ ላይ አረፈ። ዕድሜው ከስምንት አይበልጥም። ቀበጥባጣ ነው። ሌሎቹን ይረብሻል። ጠራሁትና <ልባርክህ እፈልጋለሁ> አልኩት። <ይህ ምን ማለት ነው?> አለኝ። እኔም <መባረክ ማለት በአንተ ሕይወት ይፈጸም ዘንድ መልካምን ቃል መናገር ነው> አልኩት። እናም ዓይኑን

እንዲጨፍን እኔም ስጸልይ እጆቹን እንዲያነሣ ነገርኩት:: ይህንኑ ሲያደርግ እንዲህ ብዬ ጸለይኩ:: «የሰማይ አባት ሆይ፣ ማርቲንን ለተለየ ዓላማ ስለፈጠርከው አመሰግንሃለሁ:: በእርሱ ሕይወት ለምትሠራው ነገር ሁሉ ክበር:: እኔም ማርቲንን በአንተ ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ እባርከዋለሁ»::

«እርሱም ፈጥኖ ከድንኳኑ ወጣ:: ምን እንደ ተሰማው ለማወቅ በጣም ጓጉቼ ነበር:: ሮጦ ወደ ጓደኞቹ ከሄደ በኋላ እንዲህ ነበር ያላቸው፣ 'ስሙ ወደ መድረኩ መሄድና በረከትን መጠየቅ ይገባችኋል:: በእውነት ጥሩ ነገር ነው::'»

መርገም የበረከት ተቃራኒ ነው:: በረከት ከእግዚአብሔር ሲሆን፣ መርገም ግን ብዙውን ጊዜ ከሰይጣን ይመጣል:: ከርግማን የተዋጀ ሰው በርግማን ሥር ሲኖር ማየት ደግሞ ያሳዝናል::

በመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደ ጠቀስኩት፣ «አትረባም! ዋጋ የለህም!» የሚሉ የመርገም ዜማዎችን እየሰማን አድገናል:: ይህ ግን ለእኛ ልጆች ዕድል ፈንታ መሆን የለበትም:: በቤተሰብ ደረጃ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን፣ ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን ቢባርኩ አስደናቂ ለውጥን እናያለን::

ያ ካልተሳካልን ተቃራኒው እውነት ይሆናል:: በልጆች ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው ወላጆች የሚናገሩት ከንቱ ቃል ትርጓሜው መርገም ነው::

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መርገምን «በሌላ ላይ ክፉ ነገር እንዲደርስ መመኘትና መናገር» ሲል ይፈታዋል:: እንደ በረከት ሁሉ ይህም ትውልድን የሚነካና ካልተሰበረ በስተቀር መዘዙ የማይቆም ነው::

ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸውና (ምሳ. 18:21)፣ በልጆች ላይ ስለምንናገረው ሁሉ መጠንቀቅ አለብን:: ያዕቆብ ሚስቱ ራሔልን በሞት እንደሚያሳጣው ቢያውቅ ኖሮ በቤት ራስነቱ ያን መርገም አይናገርም ነበር (ዘፍጥ. 31:32)::



እስራኤላውያን፣ «መርገሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» ሲሉ መጪውን ስቃያ አላስተዋሉም (ማቴ. 27:25):: ያ ትውልድ ሳያልፍ ቲቶ የተባለው የሮማ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ወረረ:: በረሃብ፣ በቃጠሎና መሰል መከራዎች ተናጋሪዎቹ መርገሙን አጣጣሙ:: በዚያም አልቆመም፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ብቻ ከ6 ሚሊዮን የሚበልጡ አይሁዳውያን በአሠቃቂ አኳኋን ተጨፈጨፉ::

- አንተ መቼውንም ሰው አትሆንም!
- ዱሮም የትምህርት ነገር ለአንቺ. . .
- እናንተ የማትረቡ

ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት መርዘኛ ንግግሮች ወደ ልጆች ጆሮ መስደድ ተግሣጽ አይደለም:: ርግማን ነው! ወላጁ ደደብ ያለው ልጅ በትምህርቱ ሊሳካለት አይችልም:: እነኚህ እንደ ዋዛ የተወረወሩ ቃላት በልጁ ሕሊና ላይ በመቀረጽ መላ ሕይወቱን ያጨልማሉ::

ምንጮቹ የተለያዩ ቢሆኑም እንኳ ሁሉም መርገሞች ተመሳሳይ ምልክቶች አሏቸው:: ዴሪክ ፕሪንስ የተባሉት ታዋቂ ጸሐፊና የወንጌል ሰባኪ እነዚህን ክፉ ፍሬዎች እንዲህ ይዘረዝሯቸዋል፦

1. አእምሮአዊና ስሜታዊ መታወክ፣
2. በተደጋጋሚ ለበሽታ መጋለጥ፣
3. መካንነት፣
4. የጋብቻ መፍረስና የቤተሰብ መበተን፣
5. የማያቋርጥ የገንዘብ እጥረት፣
6. ለአደጋ በተደጋጋሚ መጋለጥ፣
7. ያለ እድሜ መቀጠፍ::

ለማጠቃለል እንሞክር፤ ደጋግመን እንደ ጠቀስነው የሥልጣን ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው:: በቤተሰብ ላይ

ደግሞ ሥልጣኑ ለወላጆች ተሰጥቷል። ይህ ሊሻር አይችልም። እናም በተሰጠን ሥልጣን የፈለግነውን መናገር እንችላለን። ሲጠቃለል ግን ሁለት ነው። በረከት ወይም መርገም። ለልጆቻችን የተሻለውን እንምረጥ። በረከት!

መባረክ ከመርገም ይጠነክራል፤ እውነተኛ በረከት በተነገረለት ግለሰብ ላይ አይቆምም። ከአባት ወደ ልጅ፣ ከልጅ ወደ ልጅ ልጅ ይተላለፋል። ወሰን ገደብ የለውም። ባለፉት ዘመናት የተባረኩት የእምነት አባቶች ዛሬ ለምንኖረው ለእኛ ተርፈዋል።

* * *

ጆን. ኤች. እስታርኪ በጭካኔው የታወቀ እንግሊዛዊ ወንጀለኛ ነበር። ይህ ሰው የገዛ ሚስቱን እንኳ ሳይቀር ገድሎአል። በመጨረሻ ሲያዝ ግን ወንጀሎቹን አመነና ይሙት በቃ ተፈረደበት። የፍትሕ ባለሥልጣኖቹም የደኅንነት ሠራዊት (ሳልቬሽን አርሚ) የተባለ መንፈሳዊ ድርጅት መሥራች የሆኑትን ጄኔራል ዊልያም ቡት የእስታርኪን የቀብር ሥነ- ሥርዓት እንዲያስፈጽሙ ጠየቋቸው። እናም ጄኔራል ቡት የሰውየውን አስከፊ ታሪክ በመሸከም በብዙ ሕዝብ ፊት ቆሙ። በዘመናቸው ሁሉ በሕዝቡ ፊት የተናገሩ ቢሆንም እንዲህ ያለ የተቆጣና አስፈሪ ፊት ገጥሟቸው አያውቅም፤ የሆነ ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ቃሎቻቸው ብዙዎችን አስደንቋል። «ጆን. ኤች. እስታርኪ የምትጸልይለት እናት አልነበረችውም!» ነበር ያሉት። ለልጆቻችን እንጸልይ!



# 6

## ልጆችን ወደ እውነት መምራት

ግለሰቡ የንግድ ሰው ብቻ አልነበረም፤ የተሰጠ ክርስቲያን ጭምር እንጂ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ታዲያ በእርሱ ይሁን በአሽከርካሪው ስሕተት ባይገለጽም መኪና ይገጨውና ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ይወሰዳል። ከዚያ በኋላ የሚኖረው ዕድሜ ከሁለት ሰዓታት እንደማይበልጥ በባለሙያዎች ቢነገረውም እንኳ ይህ በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ ያለውን የጠነከረ መታመን አልቀነሰበትም። ሆኖም፣ ቤተሰቦቹን በፍጥነት አስጠራ። እያንዳንዳቸውንም በየተራ ይሰናበታቸው ጀመር።

«ደህና እደሪ ወድ ባለቤቴ፤ በፀሐይ ብርሃንና በጨለማ አብረን ብዙ ጊዜ ተንሸራሸረናል። ችግሬ ነው ባልኩት ነገር ላይ ሁሉ አንቺ የምታበረችኝ ነበርሽ። እጅግ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕያው መንፈስ በፊትሽ ላይ ሲያበራ አይቻለሁ። የእኔዋ ሙሽራ ከሆንሽበት ቀን ይልቅ ዛሬ እወድሻለሁ። ደህና እደሪ የእኔ ቆንጆ። በሚቀጥለው ዕለት ጧት አገኝሻለሁ። ደህና እደሪ።

«ደህና እደሪ ምሕረት፤ አንቺ የመጀመሪያ ልጃችን ነሽ። ለእኔ ለአባትሽ ምንኛ የደስታ ምንጭ ነበርሽ? እንዴት ዓይነት ጠንካራ ክርስቲያን ነሽ ምሕረት? አባትሽ ምን ያህል እንደሚወድሽ ሁልጊዜም አትረሺውም። ደህና እደሪ ምሕረት፤ ደህና እደሪ።

«ደህና እደር ፈቃዱ፤ የአንተ ወደ እኛ ቤተሰብ መቀላቀል ንጹሕና አስደሳች በረከትን መቀበል ነበር። እግዚአብሔርንና ወላጆችህን እጅግ የምትወድድ ልጅ ነህ። በሁሉም ክርስቲያናዊ ጸጋና መልካም ነገር ሁሉ ማደግህ ይቀጥላል።

የእኔ የአባትህ ፍቅርና በረከትም ይከተልሃል:: ደህና እደር ፈቃዱ፤ ደህና እደር::»

የትልቁ ወንድ ልጅ የፈቃዱ ተከታይ ደግሞ ቸርነት ነበር:: ተሰናባቹ አባት ከሚስቱ ጀምሮ ሁሉን በተዋረድ ያነጋገረ ቢሆንም፣ ቸርነት ዘንድ ሲደርስ እርሱን ዘልሎ ወደ መልከ መልካሚቱ ጸጋ አለፈ:: ቸርነት ከቤተሰቡ ልጆች በተቃራኒ ለክፋት ሥራ በመተባበሩ እናትና አባቱን ክፉኛ ያሳዘነ ወጣት ነው:: ስለዚህም እርሱም በመጨረሻ ሊያናግረው የወሰነ ይመስላል::

«ደህና እደሪ ጸጋ፤ የደስታ ዝማሬና የደማቅ ብርሃን ጨረር ነሽ:: ብዙም አልራቀም፤ በቅርቡ ሕይወትሽን ለጌታ ኢየሱስ ሰጠሽ:: በዚህም የአባትሽ ደስታ ሞልቶ እንደ ፈሰሰ አይተሻል:: ደህና እደሪ ትንሿ ቆንጆ፤ ደህና እደሪ::

«ደህና ሁን ቸርነት፤ እንዴት ያለህ መልካምና ተስፋ የሚጣልብህ ልጅ ነበርህ? እናትህና እኔ አድገህ ጥሩ ሰው ይወጣሃል የሚል ተስፋ ነበረን:: ለሌሎቹ ልጆቻችን ያደረግነውን መልካም ነገር ሁሉ ለአንተ አላጎደልንብህም:: የተለወጠ ነገር ቢኖር ያ ከአንተ ተግባራዊ ማንነት የተነሣ እንደ ሆነ ራስህ ልትመሰክር ይገባሃል:: በምላሽህ እጅግ አሳዘንከን:: ሰፊውንና ወደ ጥፋት የሚወስደውን መንገድ መረጥህ:: ከቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ያገኘኸውን ጠቃሚ ማስጠንቀቂያም ችላ አልከው:: የአዳኝህን ጥሪ ለመስማት አልወደድክም:: ቢሆንም፣ እስካሁን ወድጄሃለሁ:: አሁንም እወድሃለሁ:: ምን ያህል እንደምወድህ የሚያውቅ ግን እግዚአብሔር ነው:: ደህና ሁን ቸርነት ደህና ሁን፤ ደህና ሁን::»

«አባባ ሌሎቹን ደህና እደሩ ስትል ቆይተህ እኔን ደህና ሁን ያልከኝ ስለ ምንድን ነው?» አለ ቸርነት የአባቱን እጅ እጅግ አጥብቆ ይዞ እየተንሰቀሰቀ::

«ምክንያቱ ቀላልና ግልጽ ነው:: ሁሉንም የቤተሰቤን



አባላት በብሩኅ ጧት አገኛቸዋለሁ:: ለዚህም ብዙ የማይናወጡ ተስፋዎች አሉኝ:: በእነዚሁ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያሉ ቋሚ ተስፋዎች መሠረት አንተን በዚያ የማየት ዕድል ፈጽሞ የለኝም:: ደህና ሁን ቸርነት፤ ደህና ሁን» አለ አባትየው::

ከዚህ በኋላ ቸርነት በወለሉ ላይ ተንበረከከና አባቱ የተኛ በትን አልጋ ተደግፎ መጮህ ጀመረ:: ከነፍሱ በሚወጣ ሲቃ እና በልቅሶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:: ኃጢአቱን ይቅር ይለው ዘንድ::

«ከምርህ ነው? ቸርነት እርግጠኛ ነህ?» ሲል ጠየቀው አባቱ::

«አዎን፣ ጌታ ምስክሬ ነው» በማለት መለሰ ልቡ የተሰበረው ወጣት::

«እንግዲያውስ ጌታ ይሰማሃል:: መዳንም ይሆንልሃል:: እኔም የምልህ ደህና ሁን አይደለም:: ደህና እደር እንጂ፤ ደህና እደር ልጄ ቸርነት::»

አሁን ቸርነት የወንጌል ሰባኪ ነው::

* * *

እግዚአብሔርን የማወቅ ፍላጎታቸውን በማጤንና ተገቢነቱንም በማወቅ ልጆችን ወደ እውነት ለመምራት የተሻለው ቀን ዛሬ ነው! (2ኛ ቆሮ. 6:2) የግድ በሞት ጣዕር ላይ መድረስ የለብንም::

ቴድ ዋይት የተባሉት ታዋቂ አሜሪካዊ መጋቢ፣ «የታዘዝነው ለዓለም ሁሉ ወንጌልን እንድናደርስ፣ እንድናስተምርና ደቀ መዛሙርትን እንድናፈራ ነው:: ታዲያ ይህን ከልጆቻችን ብንጀምር አይሻልም?» ብለዋል::

የልጆች ቅን አመለካከት በጌታ እንዲያምኑ በር ይከፍታል:: ልባቸው ደግሞ መልካም መሬት ነው:: ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በምድራችን ካሉ አማኞች 86% ውሳኔ

ያደረጉት ዕድሜያቸው 15 ዓመት ከመሆኑ በፊት ነው:: ከ15 እስከ 30 ዓመት ዕድሜ ሳሉ ጌታን የተቀበሉት 10% ሲሆኑ፣ ከ30 ዓመት በኋላ ግን ቁጥሩ ወደ 4% አሽቆልቁሏል::

«ከ5-10 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለን ልጅ ወደ ክርስቶስ መምራት በምድር ላይ እጅግ ቀላሉ ሥራ ነው፤ መዳንን የምትነግሯቸው ልጆች ዕድሜ ዝቅ ባለ ቁጥር ተግባሩም ቀና እየሆነ ይሄዳል» የሚሉት ታላቁ ወንጌላዊና የትምህርት ባለሙያ ዶክተር አር. ኤ. ቶሪ ናቸው:: የሰባኪዎች ንጉሥ የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው ቻርልስ ስፐርጀን ደግሞ በሚገባ እስከ ተነገረው ድረስ የአምስት ዓመት ልጅ ሊያምንና ሊለወጥ ይችላል በማለት ይህንኑ ያጠናክራል::

የሕፃናት መዳን ምሥጢር ሊያስደንቀን አይገባም:: እንዲያውም ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት አንዱ ቅድመ-ሁኔታ እንደ ሕፃን መሆን ነው (ማቴ. 19:14):: ትንሿ ልባቸው ክፍት ነች:: እውነተኛና ትሑታን ናቸው:: ኃጢአተኝነታቸውን ስትነግሯቸው ያለምንም ማንገራገር ይቀበላሉ::

እምነት በቀላሉ ወደ ልጆች ይመጣል፤ ለዚህም ነው ታላላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ታዋቂ ግለሰቦች በልጅነታቸው ጌታን የመከተል ውሳኔ ያደረጉት:: ይስሐቅ ዋትስ በ9 ዓመቱ አመነ:: ጆናታን ኤድዋርድስ በ7፣ ማቴው ሔንሪ በ11፣ ጂም ኢልየት፣ ኮሬ ቴን ቡም እና ሩት ግርሃም ደግሞ በ5 ዓመታቸው ዳኑ::

ብዙ ወላጆች ልጁ ወደ ጌታ እንዲመጣ የምፈልገው ካደገና የሚያደርገውን ካወቀ በኋላ ነው ሲሉ ይደመጣሉ:: ያሳዝናል! ልጆች የሚያደርጉትን ማወቅ ያለባቸው ወደ ጌታ ከመጡ በኋላ ነው:: ኃጢአተኝነታቸውን ካወቁ በቂ ነው:: ያኔ አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉና::



በዘመናችን እየተፈጸሙ ካሉ መንፈሳዊ ስሕተቶች አንዱ ለልጆች ትኩረት አለመስጠት ነው:: ከስብከት በኋላ ውሳኔ ለሚያደርጉ ሰዎች ጥሪ ሲደረግ ወደፊት የሚወጡትን ልጆች ሲገባችሁ ትመጣላችሁ እያሉ የሚመልሱ ካሉ የሚያገለግሉት እግዚአብሔርን አይደለም::

ልጆች ያለምንም ገደብና ቅድመ- ሁኔታ በራሳቸው ውሳኔ ወደ ጌታ መምጣት አለባቸው:: ማንም ሊከለክላቸው አይገባም:: ወደ እኔ ይምጡ ብሎ የፈቀደላቸው ኢየሱስ ነውና!

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ማብራሪያ የጻፉ አንድ አገልጋይ እንደ ተናገሩት፣ «እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ይቀይራል፤ ሥራውን ግን ይቀጥላል!» አዎን፣ ነባሩ ለአዲሱ ያስረክባል:: ወንጌል ከመሮጥ አይታቀብም::

## የደኅንነት ተስፋ

ታላቁ መሪ ኢያሱ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ሲደራደር፣ «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» ብሎ ነበር (ኢያ. 22:15):: ይህን ሲል በቤተሰቡ እምነት ሳይሆን በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተደግፎ ነው:: ከዘመናት በኋላ ይኸው ተስፋ የፊልጵስዩስ እሥር ቤት ኃላፊ ለነበረው መቶ አለቃ መጣለት:: «በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ» (የሐዋ. 16:31)::

የቆርኔሌዎስ እምነት ለቤተሰቦቹም መዳን ምክንያት ሆኗል:: (ደኅንነት ከግለሰቡ ውሳኔ ጋር የተያያዘ መሆኑን አንዘነጋም::) ካትሪን ቡት፣ «ጌታ ሆይ፣ ቤተሰቤን ሳልይዝ ብቻዬን በፊትህ መቆም አልፈልግም» እያለች ትጸልይ ነበር:: ሁሉም ዳኑ:: አገልጋዮችም ነበሩ:: የእኛ እምነትና ጸሎት ብሎም ምስክርነት ለልጆቻችን መዳን መንገድ ጠራጊ ነው::

ለወደፊት ተስፋዎቻችን ደኅንነትና በሕይወት መኖር

ልንራራ ይገባል:: ልጆቻችንን እንባርካቸው:: ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅም ለአገልግሎት እንለያቸው:: እንዲህ ብናደርግ የድል ድምፅ የሚያሰሙትን ወንዶች፣ በደስታ የሚዘምሩትን ሴቶች፣ በጥቅሉም በደስታ የሚስቁትን ልጆች በመስማት ሐሤት እናደርጋለን::

* * *

## መቼ? እንዴት?

ጥያቄ:- ልጆች በክርስቶስ አምነው ሊድኑ ይችላሉ?

መልስ:- አዎን! ያለጥርጥር!

* * *

እነርሱም ኃጢአተኞች ናቸውና (ሮሜ 3:23) ክፋት በሞ-ላበት በዚህ ዘመን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ገና በለጋ ዕድሜያቸው ጌታን እንዲቀበሉ ማበረታታት ትልቅ ጥበብ ነው:: ክርስቲያን ወላጆች ይህን በተመለከተ ሰፊ ዕድል አላቸው:: ጥብቅ ኃላፊነትም አለባቸው::

አንድ ልጅ ዕድሜው ስንት ሲሞላ እንደሚድን አልተወሰነም፤ እናም በሚገባቸው ጊዜ እንዲወስኑ መጋበዝ የእኛ ፈንታ ነው:: ማለትም ኃጢአት ከእግዚአብሔር ፍላጎት ውጪ እንደ ሆነ ኃጢአተኛ መሆኑንና ጌታ ኢየሱስ እርሱን ለማዳን እንደ ሞተ ሲገባው መወሰን አለበት::

ጆሮአቸው መስማት ሲጀምር ስለ ኢየሱስ አዳኝነት እንነግራቸዋለን:: በግልጽ እንደሚታወቀው እኛ ከነበርነበት የልጅነት ዘመን ይልቅ የአሁኑ ተግዳሮት የበዛበት ነው:: ስለዚህ ልጆች በተቻለ ፍጥነት በእረኛቸው ጉያ መሸሸግ አለባቸው::

በዚህ ዘመን ያሉ ልጆች የመረዳት ችሎታ ፍጥነት



ስለሚያሳይ ለእግዚአብሔር እውነትና ለክርስትና ውሳኔ ያልደረሱ አድርጎ ማሰቡ የዋህነት ነው::

ልጆችን ወደ ክርስቶስ መምራት የምንችለው እንዴት ነው የሚለው ጥያቄ ወደ አእምሯችን መምጣቱ አይቀርም፤ ለዚህ ተግባራዊነት የሚረዳውን በልምድ የተፈተነና በተግባር የታየ ምክር ሲሰጡ፣ «ከትንሽ ጥፋቱ ተነሥታችሁ ኃጢአተኝነቱን አሳዩት:: ኃጢአተኛ መሆኑን ያላወቀ የመዳንን አስፈላጊነት አይረዳምና:: ቀጥሎ የእግዚአብሔርን ቅድስና ከሰው የኃጢአተኝነት ባሕርይ ጋር በማወዳደር የኃጢአትን ዋጋ ንገሩት፤ ያም ሆኖ እግዚአብሔር የሚጠላው ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኛን እንዳልሆነም ግለጹለት:: በመጨረሻም ለደኅንነቱ በክርስቶስ የተፈጸመውን ሥራ በማሳወቅ ለንስሐ ጋብዙት» ይላሉ የወንጌል ስርጭት ለሕፃናት ኅብረት ብሔራዊ ዳይሬክተር የሆኑት ፍራንክሊን ኤሊይስ::

## ይህን እንደሚከተለው ማብራራት ይቻላል

1. በተቻለ መጠን ልጆቻችሁ በትንሽ ዕድሜያቸው ወደ ጌታ ቢመጡ እንደሚሻል እወቁ:: ልጁ ወይም ልጅቷ የትኛው ትክክል የትኛውስ ስሕተት መሆኑን መገንዘብ ሲጀምሩ ወይም በቤት ውስጥ ስለ ፈጸሙት ጥፋት ይቅርታ መጠየቅን ሲለማመዱ ያኔ ስለ ኃጢአትና ስለ አዳኛቸው ለመንገር ጥሩ ጊዜ ነው::
2. ስለ ጌታ አዳኝነት ወይም ስለ እግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ልጆች ጥያቄ ሲያቀርቡ ያንን አጋጣሚ ተጠቀሙበት:: በጥንቃቄም አድምጣችሁ መልሱላቸው::
3. ያለማቋረጥ ስለ እነርሱ መጸለይ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ መወቀሳቸውንም ተከታተሉ:: ክርስቲያን ለመሆን

ዕድሜያቸው ገና እንደ ሆነ በማሰብ ሊታለሉ አይገባም:: እናንተ ስለ ኃጢአትና ስለ መዳን ስትነግሯቸው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በልባቸው ይሠራል:: ያኔ ጌታን ይቀበሉ ዘንድ መምራት የአሳዳጊዎች ድርሻ ነው::

4. ልጆች ሲጨነቁ ሲታዩ ጌታን ለመቀበል ይወስኑ ዘንድ ለማደፋፈር ያን ዕድል ተጠቀሙበት:: በሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ እንዲደገፉ ራሳቸውንም እንዲሰጡ እርዷቸው::

## ለውሳኔ መርዳት

ትክክለኛ ውሳኔ ላይ የመድረስን ልምድ ከእኛ ሊቀስሙ ይገባል:: እኛ የተሻለ ልምድ አለን:: እጅግ በጣም ጥሩ ውሳኔ አድርገን እናውቃለን:: ጌታን በተቀበልን ቀን!

እንዲወስኑ ነጻነት እንስጣቸው:: ይህ ግን ትክክል እስከ ሆኑ ድረስ ብቻ ነው:: ወደዚያ ይደርሱ ዘንድ ተሞክሮዎቻችንን ሁሉ የማጋራት ኃላፊነት አለብን:: ወደ ደቀ መዝሙርነት ለማሳደግ ይህ ዓይነቱ አገባብ ጠቃሚ ነው:: የዚህ ግብ በውስጣቸው ብስለትን መፍጠርና በአስፈላጊው ጊዜ በትክክል እንዲወስኑ መርዳት ነው::

በእርግጥ በእነርሱ ውሳኔ ጣልቃ የማንገባበት አንድ ቀን ይመጣል:: ይህ የእግዚአብሔር አሠራር ነው:: ካደጉ በኋላ እግዚአብሔርን ለመምሰልና እርሱንም ለማገልገል መወሰን የራሳቸው ምርጫ ይሆናል:: በዚያ ጊዜ እኛ ልንወስንላቸው አንችልም:: የምናደርገው ግን ያኔ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ዛሬ እግዚአብሔርን በመምሰል የእኛን ሕይወት ምሳሌ ማጋራት ነው:: ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ ያመነ ሕፃን የራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገዋል:: እንዴት እንደሚያነብ



ሊነገረውና የራሱ የጥሞና ጊዜ እንዲኖረውም የግድ ይሆናል:: በሚገባ ማስተማር የወላጆች ኃላፊነት ነው:: በዓለም ላይ ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ሁሉ የተሻለው አባት ለልጆቹ የሚያስተምርበት ቤት ነው የሚለው አባባልም ይህንኑ ያጠናክራል::

ካመኑ በኋላ መንፈስ ቅዱስን መሞላት አለባቸው:: ስለ ኢየሱስ እንዲያስተምራቸው ኃጢአትና የስሕተት ትምህርትንም ለማሸነፍ እንዲረዳቸው መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው ወሳኝ ነው:: የተስፋው ቃል ለልጆችም ጭምር ስለሆነ (የሐዋ. 2:39)፣ ሕፃናት መንፈስ ቅዱስን የመሞላት ተስፋ አላቸው:: በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ልጆች ኢየሱስን በነጻነት ያመልኩታል፤ ያመሰግኑታል፤ እጆቻቸውን አንሥተውና ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ወደ አርያም ሲጸልዩ ማየት ምንኛ ደስ ይላል?

አዎን፣ ይህ ስለ እነርሱ በሞተውና በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ድንቅ ነው:: ስለሆነም ልጆችን ወደ እውነት እንምራቸው:: ኢየሱስ እንዲህ ብሎአልና፣ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐንስ 14:6)::

# 7

# ማስተማርና ማሠልጠን

«ልጄን ማሠልጠን መቼ ብጀምር ይሻላል?» ስትል ጠየቀች እናት።

«ስንት ዓመቱ ነው?» አላት ሐኪሙ።

«አምስት።»

«እንግዲያው በሩጫ ሂጂ የእኔ እኅት። አምስት ዓመታት አልፈውብሻል!»

* * *

የቤቱ መሠረት የቤቱን ቋሚነት እንደሚወስን ሁሉ፣ በሕይወት የተጣለ መሠረትም ጠቅላላውን የሕይወት አቅጣጫ ይወስናል። አንድ ልጅ መማር የሚጀምረው መቼ ነው? ለዚህ የቀረቡ ሰዎች፣ «ከተወለደበት ደቂቃ ጀምሮ!» የሚል ምላሽ ይሰጣሉ።

ይህን ከተገነዘብን ዘንድ ማስተማርና ማሠልጠን የማን ድርሻ እንደ ሆነ እንይ። ብዙዎች በቤተሰብ ውስጥ ልጆችን የማስተማር ኃላፊነት የእናት ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የቤቱ ራስ የሆነው አባት ለዚህ ዋነኛ እንደ ሆነ ይናገራሉ። እናም ጉዳዩን አከራካሪ ያደርጉታል።

ልጆችን የማስተማርና የማሠልጠን ኃላፊነት ለወላጆች ተሰጥቷል፤ ከጌታ የተሰጠው ምክር አባቶች የክርስትናን መርሆ ለልጆቻቸው በቤት ውስጥ እንዲያስተምሩ ነው። ብዙ ቤተሰቦች ይህንን ጉዳይ ችላ በማለት ልጆችን ማሠልጠንን ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለትምህርት ቤት በመተው ምንም ኃላፊነት አይወስዱም። በሌሎች ቤቶች ደግሞ ልጆችን



የሚያሠለጥኑት እናቶች ብቻ ናቸው። አንዳንድ ታማኝ እናቶች ልጆቻቸውን በማሠልጠን ድንቅ ሥራ ሠርተዋል። ሆኖም፣ የመጀመሪያው የጌታ ዕቅድ ይህ አልነበረም። አባቶች በሚያስተምሩበት ጊዜ ልጆች የተማሩትን በተግባር እንዲተረጉሙ እናቶች መርዳት አለባቸው። በዚህ ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ዋናው ኃላፊነት ለአባቶች ተሰጥቷል። ብዙ አባቶች ይህንን ዋና ሥራ እንዳይሠሩ የሚያደርግ ብዙ ጉዳይ እንዳለባቸው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ከቤት ለብዙ ጊዜ በመራቅ ኃላፊነታቸው እንዲታሠር ያደርጋሉ።

እናም አባቶች ያስተምራሉ፤ እናቶች ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራሉ። ቀኑን ሙሉ ከእነርሱ ጋር ናቸውና። ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለዚሁ ርእስ ጉዳይ እንዲህ ይላል፣ «ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ተናገሩ፣ በሉአቸውም፣ በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት ይውሰድ» (ዘፀ. 12:3)። ከዚህ በመነሣት ይህ የክህነት ሥልጣን የተሰጠው ለአባት ነው ልንል እንችላለን። ምልጃ፣ ማስተማር፣ ማሠልጠን፣ መምራትና መባረክ የካህን ድርሻ እንደ ሆነ ደግሞ ግልጽ ነው።

ኢዮብ ሳያቋርጥ አንድ ነገር ይፈጽም እንደ ነበር ተጽፏል። «የግብዣውም ቀኖች ባለፉ ጊዜ ኢዮብ ምናልባት ልጆቼ በድለው እግዚአብሔርንም በልባቸው ሰድበው ይሆናል ብሎ ይልክና ይቀድሳቸው ነበር» (ኢዮ. 1:5)። አባት በልጆችና በእግዚአብሔር መካከል ስለተፈጠረው ክፍተት ምልጃ ሊያደርግ ይችላል። የምንጸልየው ጸሎት ለልጆቻችን ጥበቃ እንደ ማቆም ይቆጠራልና።

በአዲስ ኪዳንም ቢሆን ይህ እንዳልተለወጠ ከኤፌሶን መጽሐፍ እናያለን። «እናንተም አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ

አታስቆጡአቸው» (ኤፌ. 6:4):: ይህ አባቶች ከላይ የተሰጣቸውን ሥልጣን ያለአግባብ በመጠቀም ልጆችን እንዳያስቆጡ የሚያስጠነቅቅ ነው:: ያም ሆኖ ግን የማሠልጠን ኃላፊነታቸውን በግልጽ ያስቀምጣል::

እግዚአብሔር አባትነትን ያከብራል:: ስለዚህም ገና ከመጀመሪያው አባትን መረጠ:: እርሱም አብራም ሲሆን ትርጉሙ የተከበረ አባት ማለት ነበር:: ኋላ ግን አብርሃም ተባለ:: ይህም የብዙ ሕዝቦች አባት ማለት ነው:: የእስራኤል ታሪክ የተጀመረው በዚህ አባት ነበር:: እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ሲናገር፣ «ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁ» ይላል (ዘፍጥ. 18:19)::

በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ በአብ ሥር ሲሆን (ኤፌ. 3:14)፣ ኢየሱስም የዘላለም አባት ተብሎአል (ኢሳ. 9:5)::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪና ሽማግሌ ሊሆን የሚበቃ ማን ነው? ልጆቹን በጭምትነት እየገዛ ቤተሰቡን በመልካም የሚያስተዳድር ነው (1ኛ ጢሞ. 3:14):: በእርግጥም አንድ ሰው የገዛ ቤተሰቡን መምራት ካልቻለ እንዴት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ሊያስተዳድር ይችላል?

ልጆችን ማስተማር የሚጀምረው እነርሱን ከማቅረብ ነው:: ስለዚህ መልካም ቅርርቦሽ መፍጠር የግድ ይሆናል:: ቀጥሎም ኢየሱስን በሁሉም የሕይወታችን አቅጣጫ ማንገሥ አስፈላጊ ነው:: ልብ እንበል፣ ትናንሽ ዓይኖች ሁሌም እኛን ያያሉ:: ሕፃናትን የምናስተምራቸው በንግግራችን ብቻ ሳይሆን፣ በአኗኗራችንም ነው:: የእኛ ሕይወት በከበቡን ሁሉ የሚነበብ ግልጽ ደብዳቤ ነውና::

ልጆች በተሳሳተ አቅጣጫ ሊጓዙ ከሚችሉበት መንገድ



አንዱ ከወላጆቻቸው የሚያዩት የተጣረሰ አኗኗር ነው:: ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዱሳን፣ በውጪ ደግሞ ሌላ እንደ ሆኑ ይመለከታሉ:: ያንን ክፉ ምሳሌነትም ይከተላሉ::

የራሳችን የሕይወት ምሳሌነት ወሳኝ ነው:: ይህን እያዩ ወደ ጌታ ካላዘነበሉ በቀር ዓለማዊነት ይጠልፋቸዋል:: ልጆቻችን ከዓለም ሲለዩ ለማየት መጀመሪያ እኛ ከዓለማዊነት መለየት አለብን:: ልጆች ወላጆቻቸው የሚያስተምሯቸውና የሚያደርጓቸው ነገሮች መስማማታቸውን በጸጥታ ይመለከታሉ::

## ልብ አድርጉ. . .

- በጉጉትና በተደጋጋሚ ስትጸልዩ ለማየት
- ወደ አምልኮ ፕሮግራም ሁልጊዜ አብረዋችሁ ሊሄዱ
- ስለ ጌታ ዋጋ ስትከፍሉ ሊመለከቱ
- ከእናንተ ጋር የታመሙትን ሊጠይቁ
- መጽሐፍ ቅዱስን በእናንተ ርዳታ ሊያጠኑ
- ቤተ ክርስቲያንና መሪዎቿን ስታወድሷቸው ሊሰሙ
- እውነትን እንዲፈልጉና እንዲታዘዙ ስታበረታቷቸው ሊያደምጡ
- ጌታን በስጦታችሁ ስታከብሩ ሊያዩ
- በእናንተ ውስጥ ኢየሱስን ሊመለከቱ ልጆቻችሁ ይጓጓሉ!

መቼና እና የት እናስተምራቸው ለሚለው መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 6:4-9 ምላሽ አለው:: በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድህም ስትሄድ፣ ስትተኛም ስትነሣም ይላል:: ይህ

ቀኑን ሙሉ የምናደርገውን ይወክላል። ስለዚህ ሁልጊዜና በየትኛውም ቦታ ሕፃናትን ማስተማር የወላጆች ድርሻ ነው። ሁልጊዜ ከልጆች ጋር ያሉ እነማን ናቸው ቢባል መልሱ ወላጆች ነውና።

ልጆች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች መመለስ የወላጆች ድርሻ መሆኑን ከኢያሱ መጽሐፍ 4ኛው ምዕራፍ ቁጥር 21-24 መረዳት እንችላለን። እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ ኢያሱ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ 12 ድንጋዮችን ለመታሰቢያ አቆመ። ለሕዝቡም እንዲህ አላቸው፣ «በሚመጣው ዘመን ልጆቻችሁ አባቶቻቸውን እነዚህ ድንጋዮች ምንድር ናቸው ብለው ሲጠይቁ ለልጆቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ታስታውቃላችሁ. . .»

በተለይም ትናንሽ ልጆች አባታቸው ከማንም ይልቅ ጠንካራና አዋቂ እንደ ሆነ ስለሚገምቱ ጥያቄያቸውን ሁሉ ወደ እርሱ ነው የሚያመጡት። የእኔ አባት ሁሉን ነገር ያውቃል የሚለው እምነት በልጆች አእምሮ አለ። በተለየ ሁኔታ ጥላቻ ካላደረባቸው በቀር ልጆች በአባታቸው እውቀት ይተማመናሉ፤ ልጆች መጽናናትን ሲፈልጉ ወደ እናታቸው፣ ማብራሪያና ምሪት ሲፈልጉ ደግሞ ወደ አባታቸው መሮጣቸው እውነት ነው። ለዚህም ነው ዶን ኪርክባይ «በዚህ ምድር ላይ መልካሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አባት ልጆቹን የሚያስተምርበት ነው» ያሉት።

ከላይ እንደጠቀስነውና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች እንዳጠናከርነው ልጆችን የማስተማር ቀዳሚ ኃላፊነት በአባቶች ትከሻ ላይ ወድቋል። ይህንስንል ግን ሁሉን ጠቅልለን ለእነርሱ ሰጠን ማለት አይደለም። መሪው አባት ቢሆንም፣ እናቶችም ሰፊ ድርሻ አላቸው። እየቆዩ ሲሄዱ የቤተሰቡ ትላልቅ ልጆች እንኳ ታናናሾቻቸውን በማስተማር ኃላፊነቱን ይካፈላሉ።

ጢሞቴዎስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔርን ቃል ተምሮ



ነበር። አያቱና እናቱ በታማኝነት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን አስተምረውታል። ከማን እንደተማረው ጥያቄ በሚነሣበት ክፍል ላይ እነዚህን ብርቱ ሴቶች የሚያመለክት ቃል ሰፍሯል።

ይህንን ለማጠቃለል ልጆችን ማስተማር በቅድሚያ የወላጆች፣ ቀጥሎ የቤተ ክርስቲያን፣ በመጨረሻም የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው። ይህን ያለጥበብ እንዳናደርግ የእግዚአብሔር ምሪት ያስፈልገናል። ልጆች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ሁሉ በቂ ምላሽ መስጠት የግድ ነው። ልጆች እንዴት ሊሰናከሉ ይችላሉ ተብሎ ቢጠየቅ ቀዳሚ መልሶቻችን ሁለት ናቸው። አንድም የተሳሳተ ትምህርትን ሲቀበሉ፣ አልያም ትክክለኛውን ትምህርት ሳይማሩ ሲቀሩ።

## የማስተማር ጥበብ

ለልጆች ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ከእርሱ የተሰጠን ትእዛዝ ነው። ፈልገን ወደ እርሱ እናመጣቸው ዘንድ ፈቃዱ ነውና እናስተምራቸዋለን። በዚያም መሠረት እንደ አካላቸው እድገት በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ጠንክረው እርሱን ማገልገል ይጀምራሉ። ስለዚህ ተከታታይና አምንታዊ ትምህርት ዋነኛ አስፈላጊ ነገር ነው።

## አዋቂዎች እንደሚሉት ልጆች፡-

10% በመስማት

60% በመስማትና በማየት

70% በመስማት፣ በማየትና በመናገር

90% በመስማት፣ በማየት፣ በመናገርና በማድረግ ይማራሉ።

## ደግሞም ልጆች

- የሚስባቸውን ርእስ ጉዳይ ሲያገኙ
- መረጃ ሲፈልጉ
- በመማር ሂደት መጠቀማቸውን ሲያዩ
- ክህሎትን ሲመኙ
- የተማሩትን ከቀደመው ልምዳቸው ማገናዘብ ሲችሉ
- በመማሩ ሂደት ተሳትፎ ሲኖራቸው
- በትምህርቱ ደስ ሲሰኙ
- የሚወዱትና የሚያከብሩት ሰው ሲያስተምራቸው
- ለመማር የሚያበረታታቸው ሲያገኙ በርትተው ይማራሉ::

ካስተማርን በኋላ ደግሞ ሥልጠናው በልጆች ሕይወት ያመጣውን ለውጥ ለማየት ዕድል መስጠት ያሻናል:: እንዲናገሩ እንዲሠሩ::

### ስናስተምር

ልጆች ሁሉ እንደ ዕድሜያቸውና አካባቢያቸው የተለያዩ መሆናቸውን ማጤን ያሻል:: የ6 ዓመቱ ልጅ በግሉ አንድን ነገር ለማድረግ የሚጓጓ ነው:: የ7 ዓመቱ ልጅ የሚሠራውን ነገር ሁሉ በዓላማ ለመፈረጅ ይሞክራል:: የ8 ዓመት ልጅ ደግሞ መሰሎቹን ማስተባበር ይስበዋል:: ስለዚህ ልጆችን ስናስተምር ለየትኛው ዕድሜ ምን ማቅረብ እንዳለብን ማወቅ የግድ ይሆናል:: ይህ ልጆቹን ላለመጫን ስንል ብቻ የምንወስደው ጥንቃቄ አይደለም:: ይልቁንም ልጆች የማይረዱትን ነገር ማስታወስም ስለማይችሉ ይህን ስናደርግ ከከንቱ ድካም እንተርፋለን::



ከ0-2 ዓመት ዕድሜ ያሉ ልጆች መዝሙርን ይወዳሉ:: ዘምሩላቸው፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባ ቢነገራቸው እንገታቸውን ዝቅ ያደርጋሉ:: የእግዚአብሔር ፍቅር ሲነገራቸው ኢየሱስ ሕፃን ሆኖ እንደ ተወለደ ሊተረክላቸው ይችላል::

በዙሪያቸው ያለውን ዓለም እግዚአብሔር እንደ ፈጠረ ማስተማር የምንችለው ከ2-4 ዓመት ዕድሜ ላሉት ነው:: እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው፣ ኢየሱስ የቅርብ ጓደኛቸው እንደ ሆነ፣ እናትና አባቶቻቸው እንደሚጠነቀቁላቸው፣ መጸለይ እንደሚችሉና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንዲያከብሩ ልናስተምራቸው እንችላለን::

ከ4-5 ዓመት ያሉ ልጆች ሰዎችን ስለሚያምኑ ፈጽሞ ሐሰት መንገር አያሻም:: እውነትን ማስተማር ይገባናል:: ስለሚደነቁና ስለሚገረሙ የአምልኮን ምንነት፣ መወደድን ስለሚፈልጉ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ለመማርም ዝግጁ ስለሆኑ ወንጌልን ልናስተምራቸው እንችላለን::

በጥቂቱ ማንበብና መጻፍ ስለሚችሉ ከ6-8 ዓመት ዕድሜ ያሉትን ልጆች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ ማበረታታት ይቻላል:: ታሪክን ስለሚወድዱ ስለ ዮሴፍ፣ ዳዊት፣ ወዘተ. . . ብንነግራቸው እንደ እነርሱ ለመሆን ሊመኙና ከስሕተታቸው ሊማሩ ይችላሉ:: በሚገቡዋቸው ቃላት በመጠቀም ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን (ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ፣ ስለ ኃጢአት፣ ደኅንነት፣ ወዘተ. . . ) ልናስተምራቸው እንችላለን::

ከ9-11 ዓመት ያሉት በቂ እድገት ስላገኙ ስለ ኃጢአትና ፍርድ በግልጽ ሊማሩ ይችላሉ:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ መልካምና ክፉ መላእክት ልናስተምራቸው እንችላለን::

ከ12-14 ዓመት ያሉትን መሰስተኛ ሁለተኛ ደረጃዎችንም ለማስተማር የቅድመ-ጉርምስናን አካሄድ ማጤንና መገንዘብ

የግድ ይሆናል:: በየትኛውም የዕድሜ ክልል ቢሆኑም፣ ልጆችን በሙሉ ስናስተምር ማስታወስ ያለብን አንድ መንገድ አለ:: ይኸውም በሚገባቸው ቋንቋ መናገርን ነው::

ልጆች እኛ የምንፈልገውን ዓይነት ባሕርይ እንዲይዙ ማድረግ ያስቸግራል:: የምንችለው ስለ ባሕርያቸው ኃላፊነትን እንዲሸከሙ መርዳት ነው::

ለታላላቅ መንፈሳዊ እውነቶች መቼ ውስጣዊ ዓይናቸው እንደሚከፈት ወይም መቼ ጌታን ለመከተል ቁርጠኛ ውሳኔ እንደሚያደርጉ እርግጠኛ ላንሆን እንችላለን::

ጸጋን ልንሰጣቸው አንችልም፣ እንዲቀበሉት መንገዱን ማሳየት እንጂ

ስለ ኃጢአት ልንወቅሳቸው አንችልም፣ በእግዚአብሔር ቃል መምከር እንጂ

እንዲድኑ መወሰን አንችልም፣ ጌታን እንዲቀበሉ ማበረታታት እንጂ

ይህ የዘመናት ሥራ ነው:: በጸጥታ ያለማቋረጥና በደስታ. . . በእግዚአብሔር ታምነን . . . ተግተን በመጸለይና በትዕግሥትም በመመስከር ልንፈጽመው ይገባል::

አንዳንድ ወላጅ ልጁ የቤተሰቡን ስም እንዲያስከብር ለማስተማር ይሞክራል:: ዳሩ ግን ሰውየው ቅድመ-አያቶቹ ለዓመታት የጠበቁትን ስም በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሊያጠፋው ይችላል:: ለምሳሌ ያህል፣ ይሁዳ የሚለው የዕብራይስጥ ስም የተከበረ ነበር:: ትርጉሙም «ምስጋና» ነው:: በአዲስ ኪዳን ግን በአስቆሮቱ ይሁዳ ምክንያት ሰዎች ስለዚህ ስም ያላቸው አመለካከት ተበላሽቷል:: እናም ማንም አማኝ በዚህ ስም ልጁን ሊጠራው አይወድም:: ይልቅስ ማስተማር እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ነው::

ልጆች በቤት ውስጥ ከምክርና ተግሣጽ ይማራሉ:: ከዚያ በላይ ደግሞ የወላጆቻቸውን ሕይወት ያያሉ:: እነርሱንም



ይመስላሉ:: ወላጆቻቸው ለደስታና ለኃዘን፣ ለአደጋ ወይም ለግጭት የሚሰጡትን ምላሽ ያያሉ:: እነርሱም ተመሳሳይ ምላሽን ይሰጣሉ:: ልብ ብለን ካየናቸው ልጆች በሁለንተናዊ እንቅስቃሴያቸው የሚያንጸባርቁት በቤት ውስጥ ያዩትን ነው::

ወላጆች ልጆችን ስለ ደኅንነት የማስተማርና የማሠልጠን ኃላፊነት የተሰጣቸው ቢሆንም፣ በዚህ ዘመን ለቤተ ክርስቲያንና ለትምህርት ቤት ሊተዉት ሲሞክሩ ይታያሉ::

ስለሆነም በአንዳንድ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ሕፃናት በጌታ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን መሠረታዊ ትምህርት ሳያገኙ ይቀራሉ:: ልጆቹ በቤተ ክርስቲያን ስላደጉ፣ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ስለሚካፈሉ፣ አልፎ አልፎም የመዘምራን ቡድን አባላት ስለሆኑ የዳኑ ይመስላቸዋል:: ከክርስቶስ ተለይተው የጠፉ የመሆናቸውን እውነታ ተጋፍጠው አያውቁምና::

ልጆቻችንን በታማኝነት ካላስተማርናቸውና በጽድቅ መንገድ ካልመራናቸው የክርስትና እምነታችን በአንድ ትውልድ ውስጥ በቀላሉ ሊከስም ይችላል:: ስለዚህ እምነታችንን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፋችን በጣም ወሳኝ ነገር ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ማስተማርና ተገቢ የሕይወት ተዛምዶ በጣም አስፈላጊ ነው:: ዓይኖቻችን ያዩትን ነገር ሳንረሳ ለልጆቻችን ማስታወቃችን የጌታ ትእዛዝ ነው (ዘዳግ. 4:9)::

## ጸሎትና ቃሉን ማስተማር

ማርሲያ ቫንት ላንድ ይህ ትዝታ አላቸው:: የስምንት ዓመቷ ልጄ በአንድ ምሽት ጤነኛ አልነበረችም:: እናም ወደ መኝታ አብረን ሄድን:: መብራቱን ስናጠፋው ሳለ «እማ ልክ ሲጨልም እንቅልፍ እስኪወስድሽ ምንድን ነው የምትሠሪው» ብላ ጠየቀችኝ

«እጸልያለሁ» አልኳት::

«እሻ» አለች::

«እማማ አሁንም እየጸለይሽ ነው?» ከሠላሳ ሰኮንዶች በኋላ ጠየቀች::

«አዎን!» አልኳት::

«ይህን ያህል ጊዜ ምንድን ነው የምትጸልይው?»

«እግዚአብሔርን ስለ ሁሉ አመሰግነዋለሁ:: ስለ ቤታችን፣ መኝታችን፣ መጫዎቻዎቹና መጻሕፍት፣ ስለ እንስሳቱም ሁሉ የምለው ሁሉ እስኪያልቅ እጸልያለሁ::»

* * *

ልጆች ሁለት ነገሮችን በርዝመትና በጥልቀት መማር አለባቸው:: ጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ!

የቻርልስና የጆን ዌስሊ እናት የሆነችው ሱዛና ዌስሊ፣ «የእኔ ልጆች አፋቸውን የፈቱት በሐዋርያት ጸሎት ነው:: ሲተኙና ሲነሡ ይህን ይሉ ነበር:: ከፍ ሲሉ ደግሞ ለሌሎች እንዲጸልዩ አስተማርናቸው:: እየቆዩ የእምነት መግለጫን መናገርና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቃል መያዝ ተለማመዱ» ብላለች::

ልጆቿ ይድኑ ዘንድ ከሃያ ዓመታት በላይ እንደ ጸለየች የሚነገርላት ይህች ሴት በስተመጨረሻ አትራፊ ነበረች:: ፈረሰኛው ወንጌላዊ የተባለው ልጅዋ ጆን ዌስሊና ታዋቂው የመዝሙር ደራሲ ቻርልስ ዌስሊ ከአደባባይ የወንጌል ስርጭት አልፈው በእንግሊዝ ምድር ለተነሣው መነቃቃት ምክንያት ሆነዋል::

ከእናታቸው የተማሩት ጸሎት እጅግ የዘለቀው ጆን ዌስሊ በቀን ቢያንስ ለሁለት ሰዓት ይጸልይ እንደ ነበርና ከዚያ ሲወጣ ፊቱ ያበራ እንደ ነበር መዛግብት ያወሳሉ::

ሱዛና ዌስሊ ልጆችዋን በማሠልጠንና ማስተማር ብቻ



የተወሰነች ሴት አልነበረችም:: ይልቁንም በሳምንት አንድ ቀን ጊዜ ወስዳ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ታነጋግራቸው ነበር:: በአንድ ወቅት ለባለቤቷ በጻፈችው ደብዳቤ ላይም፣ «ሰኞ ሞሊ፣ ማክሰኞ ሔቲ፣ ረቡዕ ናንሲ. . .» የውይይት ተረኞች እንደ ሆኑ ገልጻለች::

ያለ እግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ አይቻልም:: ስለዚህ ለልጆች መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ተገቢ ነው:: በቆይታ የተሻለ እውቀት ያላቸው ታላላቆች ለትናንሾቹ ታሪክ ሲያካፍሉ መስማት ደስ ያሰኛል:: ከሥዕላዊ ታሪኮች ተነሥተው ልጆች ከፍ ወዳሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መጻሕፍት ከዚያም ወደራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ሊሸጋገሩ ይችላሉ::

ዘዳግም 6:6 «እኔም ዛሬ የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፣ ለልጆችህም አስተምረው» ስለሚል፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ከእግዚአብሔር ቃል ማስተማራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው::

ለልጆች ማስተማር ማለት ማንኛውንም ሰው ከማስተማር በብዙ ይለያል:: እነርሱን ማስተማር በሚገባቸው መንገድ ማብራራት ነው:: ይህ ደግሞ ጊዜን ይጠይቃል:: ከእነርሱ ጋር ጊዜ ይኑረን:: ልጆቻችሁን ዛሬውኑ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ክበቧቸው:: ካደጉ በኋላ ይህ ዕድል አይኖራችሁም::

ቻርልስ. ኤም. ሺልደን «በእርሱ ፍለጋ» በሚለው መጽሐፉ የሚታወቅ ክርስቲያን ነው:: ስለ ቤተሰብ የጥሞና ጊዜ አስፈላጊነት ሲተነትን እንዲህ ይላል:-

«ከቁርስ በኋላ የነበረንን የቤተሰብ የጥሞና ጊዜ ፈጽሞ አልዘነጋውም:: እንሰባሰባለን፤ አባባ ከዕለቱ የንባብ ክፍል ሁለት ቁጥሮችን ያነባል:: እማማ ሁለት ትጨምራለች:: እኛም በየተራ የዚያኑ ያህል እናነባለን:: አምስት ዓመታት ሳይቆጠሩ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ አምስት ጊዜ አነበብነው:: ራእይን ስንጨርስ ወደ

ዘፍጥረት እየተመለስን እንቀጥላለን። በዚህም ለእግዚአብሔር ቃል ያለኝ ፍቅር እየበረታ ሄደ። በአንድ ወቅትማ የማቴዎስን ወንጌል ከሞላ ጎደል በቃሌ አወጣው ነበር። ንባቡን ስንጨርስ ከዘመርን በኋላ ተንበርክከን እንጸልያለን። አባባም በስማችን እየጠራ ይጸልይልናል። አድጌ ወደ ኮሌጅ ከገባሁ በኋላ ሌሎቹ ባልንጀሮቼ የሚያደርጉትን ክፋት ለመፈጸም ተገፋፍቼ ነበር። ሆኖም በውስጤ የታመቀው የቃሉ ኃይል አበረታኝ።»

በምንም መንገድ ከሚያገኙአት ትንሽ ገቢ አሥራት እንዲያወጡና በሚችሉም ጊዜ መባ እንዲያቀርቡ ለልጆች ማስተማር ጥሩ ነው። የሚሰጡት ጥቂት ነገር ለእግዚአብሔር ሥራ እንደሚውል ሲያውቁ ደስ ይላቸዋል።

እንግዶችን በቤታችን መቀበል (በተለይም አገልጋዮችንና የወንጌል መልእክተኞችን) መልካም ነው። በረከትን እንቀበልበታለን። ልጆችም ከእንግዶቹ መልካምን ነገር ይማራሉ።

## መታዘዝና ቅጣት

ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር በፍቅር የሚያሠለጥኑ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸውን ወላጆች የማግኘት መብት እንዳላቸው ሁሉ ኃላፊነቶችም አሉባቸው። ቀዳሚ ኃላፊነታቸውም ለወላጆቻቸው መታዘዝ ነው (ኤፌ. 6:1)። ደስ በሚላቸው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በሁሉ መታዘዝ አለባቸው። ለጌታ የሚገዙ፣ እርስ በርሳቸው የሚዋደዱና ልጆቻቸውንም የሚወዱ ወላጆች የተሳሳተ ነገር እንዲያደርጉ አይጠይቁአቸውም።

አንድ ሠራዊት የሥልጣን ተዋረዶች ባይኖሩት ግራ እንደሚጋባና እንደሚተራመስ ሁሉ፣ በኅብረተሰብም አንዱ



ለአንዱ ካልተገዛ በቀር ማኅበራዊ ቀውስ ይከሰታል። እግዚአብሔር ልጆቻቸውን እንዲያሠለጥኑና በፍቅር እንዲቀጧቸው ለወላጆች ሥልጣንን ስለ ሰጠ ልጆች ለወላጆቻቸው መገዛት አለባቸው።

በእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ሆነው ከሰፈሩ ነገሮች አንዱ ልጆች መታዘዝን መማር እንዳለባቸው ነው። ይህም ከቤት ውስጥ መጀመር አለበት። አንድ የትልቅ ቤተሰብ እናት ሲናገሩ፣ «አንድ ሕፃን ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ መታዘዝን ካልተማረ እርሱን ማሠልጠኑ አስቸጋሪ ይሆናል» ብለዋል። ብዙ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን ምንም የማያውቁ አድርገው ያዩአቸዋል። እናም ትምህርቱን ሲያድጉ ለመስጠት ይዘጋጃሉ። በሚገባ የተማሩና በክትትል ያደጉ ልጆች ያሉበት ቤት የተባረከ ነው። ከጠብ፣ ከክርክርና ከጭቅጭቅም ነፃ ነው፤ ደስተኛ ቤተሰብ!

ወላጆቹን መታዘዝ ያልተማረ ልጅ ማንኛውንም ዓይነት ባለሥልጣን በመታዘዝ ያድጋል ማለት ዘበት ነው። መምህሮቹን፣ ፖሊስን፣ የሥራ አለቆቹንና የበላዮቹን ሁሉ አይታዘዝም። በማኅበረሰባችን ውስጥ አለመታዘዝን የምናይ ከሆነ ይህ በቤት ውስጥ ያለውን ያለመታዘዝ ያመለክታል።

በመታዘዝ ውስጥ ልጆችን ስናስተምር ልብ ልንላቸው የሚገቡን ነገሮች አሉ።

ሀ. ለአቅማቸው የሚመጥን ትእዛዝ ስጡ።

ለ. ትእዛዙ መፈጸሙን በሚገባ ተከታተሉ።

ሐ. ትእዛዝ አታብዙ፤ የተወሰነ ይሁን።

መ. ልጆች እያወቁ አንታዘዝም ካሉ ተግሣጽና ቅጣት ይገባቸዋል።

ብዙ ጊዜ ልጆችን የሚቀጣው አባት ቢሆንም፣ እናትም የዚሁ አካል መሆን አለባት። ይህ ካልሆነ ልጆች ለከለላ ወደ እናታቸው ጉያ ይሮጣሉ።

ልጆችን በማሳደግ የሥልጠና መርሆና ቅጣት ላይ ባልና ሚስት መስማማታቸው እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው:: በሚቀጡበት ዘዴ ላይ ሁለቱ ሊነጋገሩ ይገባል:: ውሳኔያቸውም በእግዚአብሔር ቃል ላይ በጥብቅ የተመሠረተ ደግሞም ቋሚ መሆን አለበት::

«ልጄን ለመምታት እስከማልችል ድረስ ከመጠን በላይ እወደዋለሁ!» ሲሉ የሚደመጡ ዘመናዊ ወላጆች አሉ:: እውነታው ግን ራሳቸውን የሚወዱ እንጂ በእውነት ለልጆቻቸው የማያስቡ መሆናቸውን ይጠቁማል:: «በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፣ ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል» (ምሳሌ 13:24)::

የእግዚአብሔር ቃል ተግሣጽና ቅጣትን በተመለከተ በተደጋጋሚ ይናገራል:: ጥቂት ምሳሌዎችን እነሆ:-

1. ልጆቻቸውን የሚወድዱ ወላጆች ይገሥጹአቸዋል (ምሳሌ 13:24)::
2. ተግሣጽ ያላገኘ ልጅ ከፊቱ ሞት አለ (ምሳሌ 19:18)::
3. ልጆቻቸውን የሚቀጡ ወላጆች ያርፋሉ (ምሳሌ 29:17)::
4. ልጆቻቸውን ያልቀጡ ወላጆች ያፍራሉ (ምሳሌ 29:15)::

ወላጆች የሚበይኑት ቅጣት ንዴታቸውን ለማብረድ ሳይሆን ልጆችን ለማሻሻል የታለመ መሆን አለበት:: ልጁ ከተቀጣ በኋላ ደግሞ ምክንያቱ ሊነገረው የግድ ነው::

ቅጣት በዓይነቱ የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ ልጆች አልታዘዝ ሲሉ ወይም እንቢታን ሲያሳዩ ይህን ማድረግ እንዳለባቸው በጽናት መንገር ይገባል:: ወይም ይህ እስኪገባቸው የሚፈልጉትን ነገር ሊከለከሉ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ በበትር (ልምጭ ብንለው ይሻላል) ለመምታት ትወስኑ ይሆናል:: ያኔ የምትመቱት የልጁን ጭንቅላት፣ ፊት፣ እጅ ወይም እግር አይደለም፣ ፈጽሞ አይደለም! መቀመጫው ላይ ነው::



በዕድገታቸው ዘመን ሁሉ ማስተማርና ማሠልጠኑ ይቀጥላል:: ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ነጥቦች በርካታ ናቸው:: ቀጣዩቹን አምስት አሳቦች ግን ፈጽሞ አትዘንጉ::

ሀ. *ሌሎችን እንዲፈሩ ወይም እንዲሸሹ አታድርጓቸው:-* ዙሪያችን የተከበበው በማያምኑ ሰዎች ሊሆን ይችላል:: የእነዚህን ሰዎች ማንነት ለልጆች የምንገልጸው በጥበብ እንጂ፣ «እናንተ ዓለማውያን ናችሁ፤ ወደ ቤታችሁ አልገባም!» ብለው ለመናገር በሚደፍሩበት አኳኋን አይደለም:: ከዓለም ባይሆኑም በዓለም ናቸውና አድገው ሥራ ሲይዙም ቢሆን ከዓለማውያን ጋር መገናኘታቸው አይቀርም::

ለ. *እንዲያነጋግሯችሁ ፍቀዱ:-* ትናንሽ ልጆች ሳሉ እየኮረኮራችሁ ታጫውቷቸው ነበር:: ከፍ ሲሉ ግን አኳኋኑ ይቀየራል:: ልትተኙ ስትሉ አጫውቱን ብለው ሊጠይቋችሁ ይችላሉ:: አትከልክሏቸው::

ሐ. *የአገልጋይ አመለካከት እንዲኖራቸው እርዷቸው:-* የአገልጋይ አመለካከት ከራስ ወዳድነት ተቃራኒ ነው:: ራሱን የሚወድ ልጅ ግፊትን መቋቋም አይችልም::

መ. *ለእነርሱ የምትሰጡትን አገልግሎት መዝኑ:-* የምታደርጉላቸው ሁሉ ለልጆቻችሁ መልካም ቢሆንም፣ ከራሳችሁ ዝንባሌና አመለካከት ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም አለባችሁ:: የወላጆች ዓላማ ልጆቻቸውን ደስ ማሰኘት አይደለም:: እግዚአብሔር ወደ ደስታ ይመራሉ የሚላቸውን ነገሮች መስጠት እንጂ::

ሠ. *ከውጪ ሳይሆን ከውስጥ አሳድጓቸው:-* ልባቸውን የሚያሰፋ ነገር ማስተማር እንጂ ሕግ መደርደር አያንጽም:: በእርግጥ ልጆች በርካታ መመሪያዎች የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም፣ ቀንበር እንዲሆንባቸው ግን አይመረጥም:: ዓላማው ለጌታ ኢየሱስ ካላቸው

እውነተኛና ጥልቅ ፍቅር የተነሣ ራስን መግዛት እንዲለማመዱ ነው።

ልጆችን በማስተማርና በማሠልጠን የሚገኙ ግቦች ምንድን ናቸው? ይህ ተገቢ ጥያቄ ነው። ተገቢውን ትምህርትና ሥልጠና ካገኙ ልጆች ሕይወት ቢያንስ አራት የሚያህሉ ፍሬዎችን መሰብሰብ ይቻላል።

1. *ይታዘዛሉ፦* ከላይ እንደተብራራው ልጆች መታዘዝን መማር አለባቸው። ትምህርትን እስካልጨበጡ ድረስ ተጽፎ በማየታቸው ብቻ ልጆች ይህን ተግባራዊ አያደርጉም። ሳሙኤል በሌሊት ከሞቀ አልጋው እየተነሣ ሽማግሌውን ካህን ዔሊን ለመታዘዝ ይሮጥ ነበር። በዚያ ታሪክ ውስጥ የምንመለከተው ገና ከወላጆቹ ጋር ሳለ መታዘዝን የተማረ ብላቴና ነው። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሲያገለግልም በዚያው ዓይነት መታዘዝን ቀጠለ።
2. *እግዚአብሔርንና ሰዎችን ያከብራሉ፦* እግዚአብሔርን ማክበርና መፍራት የተማሩ ልጆች ወላጆቻቸውንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያከብራሉ። ይህ አክብሮታቸው ወደ ሽማግሌዎችና ባለሥልጣናትም ይዘረጋል። በንግግርና በትምህርት እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው ምሳሌነት ይህን ተምረዋልና።
3. *እውነተኞችና ታማኞች ይሆናሉ፦* ልጆች በተለይ ስሕተት ከፈጸሙ በኋላ ያንን ለመሸፈን ሲሉ መዋሸት ትልቁ ፈተናቸው ነው። ልጆች እውነትን እንዲናገሩ ልንገፋፋቸው ይገባል። ታማኝነትንም ደግሞ መማር አለባቸው። ልጆች አንድ የሚወዱት ነገር ካዩ የራሳቸው ለማድረግ እንዲችሉ ይደብቁታል። ድርጊቱ ግን ስርቆት ነው። ይህ እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን ካወቁና የሌሎችንም ንብረት ማክበርን ከተረዱ ግን ያልፉታል።
4. *ኃላፊነትን መቀበል ይችላሉ፦* ልጆች በለጋነታቸው የሥራን ዕውቀት ይቀስማሉ፣ ኃላፊነትንም መሸከም ይለምዳሉ፤



ትናንሽ ሥራ ከተሰጣቸውና ያንንም እንዲሠሩ ከተተወላቸው ኃላፊነትን ይማራሉ። በተለይ በቤት ሆና ይህን መቆጣጠር የምትችል ደግሞ እናት ነች። ስለዚህም እግዚአብሔር ጥበብና ጥንካሬን ይሰጣታል።

## ከልጆች ምን እንማራለን?

ልጆች ስጦታን ለመቀበል የተዘጋጁ ናቸው። ተንኰልም የለባቸውም። ልብ ብለን ከተመለከትናቸው ከእነርሱ የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ትሕትና ነው። አንዲት አውክዬ ማይኔማ የተባለች ጀርመናዊት ዓለም አቀፍ የሕፃናት አገልጋይ እንዲህ አለች፣ «በመንግሥተ ሰማያት ያለው በር በልጆች ቁመት ልክ ነው፤ እነርሱ እንደ መጡ መግባት ሲችሉ፣ ዐዋቂዎች ግን ጎንበስ ማለት ይጠበቅባቸዋል!» ይህን አባባል የትሕትና ተምሳሌት አድርጋ እንደ ተናገረችው ግልጽ ነው።

ትሕትና ማለት በአጭሩ ራስን መቀበል፣ ራስን ማወቅና ራስን መሆን ነው። አንድ ጨዋ የሆነ ሕፃን ልጅ የትሕትና ባሕርያት የሆኑት ታማኝነት፣ ጥገኝነትና ሌሎችን ደስ የማሰኘት መሻት፣ ስግብግብ አለመሆንና ከጉረኝነት መራቅ የመሳሰሉ በጎ ጎኖች ይኖሩታል።

አንድ ሕፃን በሌሎች የመደገፍ ዝንባሌው ግልጽ ነው። በአባቱና ዘመዶቹ ይታመናል። ይህም *እምነትን* ያስተምረናል። ልጆች አያስመስሉም፤ የሆኑትን ናቸው። ከዚህም የተነሣ *ግልጽነትን* ያስተምሩናል። ሐቀኞች ናቸው፤ አያታልሉም። ለእኛም *እውነተኝነትን* ያሳዩናል። ለማወቅና ለመማር ይፈልጋሉ። ስለዚህም ሁልጊዜ ይጠይቃሉ። ከእነርሱ *ትጋትን* መማር እንችላለን።

የሚያስደንቀውና ብዙዎቻችንም ልብ የማንለው የልጆች ብርቱ ጎን ደግሞ ጽናት ነው። በሚገባ ለተረዱትና ላመኑበት ነገር ልጆች ዋጋን ይከፍላሉ። ለጌታ ሥራ ከእኛም ይልቅ

ቅንዓትና ጽኑ ፍላጎት አላቸው። የራሳቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመጋፈጥም ድፍረት አያንሳቸውም።

ታንያ ብራይተን የተባለችው የወንጌል መልእክተኛ በኡጋንዳ ቆይታዋ የተማረችውን የልጆችን ጽናት የሚጠቁም ገጠመኝ እንዲህ ትተርካለች። «ለአንድ ዓመት ካስተማርኩበት የተለየ ትምህርት ቤት ውስጥ አንዱ ክፍል ፈጽሞ አይረሳኝም። ወላጆቻቸውን በኤድስ የተነጠቁ ሕፃናት ነበሩበት። ውስጣቸው በዝምታ ይጮሃል። በምድር ላይ የሚቆዩበትን ጊዜና ምክንያትም አያውቁም። ከመካከላቸው ደግሞ እጅግ የተለየች ልጅ ነበረች። ስሟ ሩት ይባላል።

«ሩት እድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ነው። ወላጆቿ ሞተዋል። በዕድሜ ዘመኔ ሁሉ እንደ ሩት ብርቱ ልጅ አላየሁም፤ በደንብ ሳላውቃት በፊት ከተማሪዎቼ እንደ አንዷ ብቻ ነበር የማያት። በክፍል ውስጥ የምትቀመጠው ፊት ለፊት ሲሆን፣ በጉጉትና በተመስጦ ትምህርቷን ትከታተላለች። አንድ የተለየ ነገር ብቻ ነበራት። ራስዋን ትከናነባለች። ምናልባት ሙስሊም ትሆን ብዬ ራሴን ጠይቄ አውቃለሁ። በዚህ ሞቃት አገር ራስን መሸፈን ምን ይባላል? ግን ደግሞ ስትዘምር ፊቷ በብሩህ ፈገግታ ይደምቃል። በልቧ የሞላው ደስታ በሁለመናዋ ሲፈስ ይስተዋላል።

«ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሩት ከትምህርት መቅረትን አዘወተረች። አንድ ቀን በመንገድ ስሄድ በአንድ ግድግዳ ጥግ በተወሸቀ ደረጃ ላይ ተቀምጣ አየኋት። ፊቷን በእጆቿ ሸፍናለች። እናም ወደ እርሷ ተጠግቼ ምን እያደረገች እንደሆነ ጠየቅኋት። 'ጤንነት አይሰማኝም መምህርት ታንያ?' አለችኝ። እኔም ሕመምዋ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ፈለግሁ። አስከፊውን እውነታ ነገረችኝ። የኤድስ በሽተኛ ነበረች። ለካስ ራሷን የምትሸፍነው እኔ እንዳሰብኩት አይደለም። በቁስልና ጠባሳ የተሞላ ስለነበር የሌሎችን ሽሙጥ ፈርታ ነው።



አንገቷ ማበጡንና እጆቿም እንደ ተዥጎረጎሩ ልብ ብዬ ተመለከትኩ።

«ስትነግረኝ ዓይኖቿ በእንባ ተሞልተው ነበር። ብቸኝነት ከብቧታል። የተጣለች መሆኑ ክፉኛ ይሰማታል። ዘመዶቿ አይወዷትም። ሊያቀርቧትም አይፈልጉም። ያ የተቀመጠችበት ደረጃ የእርሷ ብቸኛ መሸሸጊያ ስፍራ ነው። የምትጽናናው እዚያ፣ የምትሸሸውም ወደዚያ ነው። በዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ እንዴት ወላጆቿን በዘመኑ መቅሰፍት እንዳጣች አጫወተችኝ። በንግግሯ መጨረሻ ግን ሩት የዳነች መሆንዋንና ኢየሱስ ከእርሷ ጋር ስለሆነ በምንም እንደማትፈራ በብርቱ እምነት አስረዳችኝ፤ አምርሬ አለቀስኩ።

«በኋላም ወደ ትምህርት ገበታዋ ተመለሰች። በትጋት መከታተል፣ በእምነት መጸለይና በምስጋና መዘመርን ቀጠለች። ከቆይታ በኋላ ግን ያቺን ጓደኛዬን የማላይበት ጊዜ መጣ። ተሰወረች። «ሩት ወደየት ሄደች?» ብዬ ሌሎቹን ተማሪዎች ጠየቅሁ። እነርሱም ታማ አልጋ ላይ መዋሏን አረዱኝ።

«የዕለቱ ትምህርት እንዳበቃ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል ሄድኩ፤ ሩትንም በአልጋዋ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስታነብ አገኘ ኋት። ከእርሷ በታች ከ10 የማያንሱ ሕፃናት ተቀምጠው ያዳምጧታል። እግዚአብሔር መከራ በሕይወታችን እንዲያልፍ እንዴት እንደሚፈቅድ ከመዝሙረ ዳዊት ታነብላቸዋለች። ከዚያም አያይዛ በሰልፍ ውስጥ ብንሆንም እንኳ ኢየሱስ አብሮን እንደ ሆነና ለሁሉም ነገር ዓላማ እንዳለው ነገረቻቸው። ከዚያም አብረዋት ከጸለዩ በኋላ፣ 'አሁን በቅርቡ አሁኑኑ፤ ንጉሡን ልናይ እንሄዳለን። በዚያ ለቅሶ ሞትም የለም'» በማለት አንድ አዝማች ዘመሩ።

«ከጆርባቸው ቆሜ መንሰቅሰቅ ጀመርኩ። ይህችን የተወደደች ልጅ ወደ እኔ ሕይወት ስላቀረባት እግዚአብሔርን

አመሰገንኩ:: ጽናቷ ታላቅ ነበር:: በእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ ላይ የነበራት እምነት አስደናቂ ነው፤ የምትጠቀምበት ጥበብ ከዕድሜዋ የራቀ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ብቻ መገኘቱ አያጠራጥርም::

«ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሩት ጋር ያለኝ መቀራረብ እያደገ ሄደ:: እርሷ አብራኝ ስትሆን ደስታ ይሰማኛል:: እጽናናለሁ፤ ከሩት ጋር ስለ መንግሥተ ሰማያት ማውራት፣ በክርስቶስ ስላለን ተስፋ መዘመር፣ በጥቅሉ አብሮ ማሳለፍ በጣም ደስ ይለኛል:: እግዚአብሔር በእርሱ ፈጽሜ እንድታመን ያስተምረኝ ዘንድ ይህችን ልጅ ተጠቀመ:: በእኔ ሕይወት ያለውን ዕቅድና ዓላማ እንዳልጠራጠር አስተማረኝ፤ በእድሜዬ ሁሉ ተናግሬው እንደ ሆነ እንጂ ቀምሼው የማላውቀውን መከራ በእነዚህ ልጆች ሕይወት አሳየኝ:: እግዚአብሔር በተአምር ሕይወቴን ይለውጥ ዘንድ በተለይም የዘጠኝ ዓመቷን ሩት ተጠቀመ:: መምህሯ እኔ ነበርኩ:: ግን እርሷ ያስተማረችኝ ጽናት እጅግ በለጠ::»

## ማጠቃለያ

በእውቀታችሁ ብርታትና በሌሎችም ጥበብ አትጓዙ:: በእግዚአብሔር መንፈስ ብትመሩ ያኔ እርሱ በእናንተ አዲስን ነገር ያደርጋል:: ወላጆች፣ የልጆች መምህራንና አገልጋዮች ሁሉ የተመረጣችሁ ዕቃዎች ናችሁ፤ ይህንን አትርሱ:: በሕይወታችሁ ላለው የጌታ ጥሪ ታዘዙ፤ ሕፃናትን ወደ እርሱ አምጧቸው:: እርሱ እንደ ወደዳቸው እናንተም ውደዷቸው:: ግልገሎቹን አሰማሩ:: በእናንተ ተጠቅሞ ጌታ ልጆችን ወደ ራሱ እቅፍ ይሰበስባል፤ በየቆሻሻ መጣያው የሚንከራተቱትን አምጥታችሁ በእርሱ ጥበቃ ሥር አደራ ታኖራላችሁ:: በበረሃ ውኃ ጥም የተቃጠሉትን ጠርታችሁ ወደ እርሱ የሕይወት ውኃ ታስጠጋላችሁ:: ጌታ ልቅሶአቸውን ሰምቷልና! ለዚህ መከር ብዙ ሠራተኞችን ይፈልጋል:: አዲሱን የወይን ጠጅ



ሞልቶባቸው ይልካቸውም ዘንድ የታመነ ነው::

ሙሽራው ፈጥኖ ይመጣል:: ከእኛ ጋር አብረው ይቀበሉት ዘንድ የሕፃናትን ልብ እናዘጋጅ:: በኢየሩሳሌም መቅደስ ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ብለው እንደ ጮኹት ሕፃናት ይህም ትውልድ ጌታን ሊቀበል ይገባዋል!

ልጆቻችን የተወለዱት ያሉበትን ትውልድና አገራቸውን ለመቀየር ነው:: እነርሱን ደቀ መዝሙር በማድረግ ታሪክን እንቀይር:: የነገዎቹ ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና አስተማሪዎች እነርሱ ናቸው:: በጥቅሉ የዛሬ ልጆች የ11ኛው ሰዓት የመከሩ ሠራተኞችና በኃይል የተቀቡ የወንጌል መልእክተኞች ናቸው::

## የርእሱ ማብራሪያ

ሰዎችን ከዘላለም ሞት ማዳን የሚችለው ስለ እነርሱ ኃጢአት የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እርሱ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል 14ኛ ምዕራፍ ቁጥር 6 ላይ እንዲህ ብሎአል፣ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::»

እናም ልጆችን ወደ እውነት መምራት የሚለው የመጽሐፉ ርእስ ሌላ ፍች የለውም:: ወደ ክርስቶስ ማምጣት እንጂ::

# ማጣቀሻዎች

1. Emi Carmichel- Children in Crisis
2. ልጆቻችን መጽሔት (በአ/አ/ሙ/ወ/አ/ቤ/ክ/ ክፍል ሁለት የልጆች አገልግሎት የተዘጋጀ -ነሐሴ 1984)
3. Pray magazine (January- February 1998)
4. የአዘጋጁ ቃለ ምልልስ ከጀርመናዊቷ አውክዬ መይኔማ ጋር (personal interview with Awkje Meinema) የታተመ መጽናናት ጋዜጣ
5. Bill Wilson – Whose Child Is This ?
6. ገነት ጫኔ- የልጆች ባሕርይ (ለእሑድ ት/ቤት አስተማሪዎች ሥልጠና በተለያዩ ሰዎች የተዘጋጀ)
7. Sword of the Lord (June 26, 1998)
8. «ለልጆች እንጸልይ» በዓም ዙሪያ የተሠራጨ በራሪ ወረቀት
9. Teaching Children the Bible- by Genny Dairis and Fred Heifner
10. ቃለ ምልልስ ከሬቨረንድ ጂየሪ ኩክ እና መጋቢ ጌሪ መንሰን ጋር -ያልታተመ (Personal interview with Pastor Gerry Menson and Rev. Gerard (Jerry) Cook – Shiloh Christian Fellowship)
11. George B. Eager- How to Succeed in Winning Children to Christ.
12. የሕፃናት ድምፅ መጽሔት (በሕፃናት ደኅንነት ጥበቃና ጥቃት ተከላካይ ማኅበር የሚዘጋጅ - ሰኔ 1997 እ.ኤ.አ)
13. Margaret (Bailey) Jackobson- The Child in the Christian Home.
14. ተስፋዬ ተሾመ - የልጆች ሥነ ልቦናና ክርስትና (ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባዔ የቀረበ)



## ስጦታ

ከ ______________________________

**From** ..........................................................

ለ ______________________________

**To**..................................................................

ቀን ______________________________

**Date**...............................................................

ፊርማ ______________________________

**Signiture**.........................................................

# ምስጋና

መጽሐፉ ከግል ይልቅ የጋራ ሥራ ነው ቢባል አይጋነንም:: በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጽሑፉ ለኅትመት እንዲበቃ የረዱኝ ወገኖች አሉ::

ፓስተር መርዕድ ለማ፣ ወንድም ዓለማየሁ በቀለ፣ ወንድም ካሣዬ ኃይሌ እና ወንድም ጌቱ አማረ ጥቂቶቹ ናቸው::

ወንድም ንጉሤ ቡልቻና እኅት ገነት ጫኔ ረቂቁን ተመልክተው አስተያየታቸውን አስፍረዋል:: ሩት መኮንንና ወንድም ገዛኸኝ  አንበሉ ደግሞ ያለቦታቸው የተሰነቀሩ ፊደሎችን ለቅመዋል::

ወንጌላዊ መድኅን ገ/ሥላሴ፣ ወንድም ዘነበ ገ/ሐና፣ ወንድም ገዛኸኝ ሙሴና ወንድም ናሁሠናይ አፈወርቅ ለኅትመት የተዘጋጀውን ጽሑፍ ተመልክተው ያደረጓቸው ለውጦች እጅግ ጠቃሚ ነበሩ:: የእኅት  ተናኘ ለማ ግልጽና ጠንካራ እርማት ቅርጸቹን እንድቀይር ረድቶኛል:: ሁሉንም ከልቤ አመሰግናለሁ::

እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

ጸሐፊው